ሥ.

ማውጫ ገፅ

መግቢያ...1
1. የዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም...3
1.1. መከላከል ...3
1.1.1. የመረጃ ትምህርትና ስርፀት እንዲሁም ቁሳቁስ ስርጭት...3
1.1.2. የኮንዶም ስርጭት ...6
1.1.3. የአባለዛር በሽታዎች ህክምና ...7
1.1.4. በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክክርና የምርመራ አገልግሎት ...8
1.1.5. ከእናት ወደ ልጅ የቫይረሱን መተላለፍ መከላከል ...9
2. የድጋፍና እንክብካቤ...10
2.1 ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ፣ ወላጆቻቸውን ያጡና ተጋላጭ ህፃናትና ልጆች ...10
2.2 የቤት ለቤት እንክብካቤ ስልጠናዎች ...12
2.3 የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መድሃኒት ተጠቃሚዎች ...13
3. አቅም ግንባታ ...13
3.1 የማህበረሰብ ውይይት ...14
3.2 የሜይነስትሪሚንግና ፓርትነርሽፕ ...16
3.2.1 የሜይነስትሪሚንግ...16
3.2.2 ፓርትነርሽፕ...20
3.3 ሌሎች ... 20
4. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማኅበራት ተሳትፎ ...21
4.1. የበጀት ድጋፍ የተደረገላቸው መያዶች ...24
5. ፕሮጀክት ምዘና ...25
5.1. ከምግብ ዋስትና ለአስተያየት የተላኩ ፕሮጀክት/ፕሮፖዛሎች...25
5.2. የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄ የቀረበባቸው ፕሮጀክት/ፕሮፖዛሎች ...26
6. ስትራካጂክ እቅድ...28
7. የበጀት ምንጭ አጠቃቀም ...29
8. ክትትልና ግምገማ...30
9. አስተዳደር ነክ ተግባራት...33
10. ያጋጠሙ ችግሮች...34
11. የታዩ መልካም የስራ እንቅስቃሴዎች ...35
12. አባሪ ሠንጠረዦች...36

## መግቢያ

የአብክመ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት በ1998 በጀት አመት በተለያዩ ፈፃሚ አካላት በእቅድ ተይዘው ሊተገበሩ የሚችሉ የተለያዩ ስራዎችን በበጀት በመደገፍ በየደረጃዉ በርከታ የፀረ-ኤድስ ሥራዎች ተከናዉነዋል፡፡
በ 1998 በጀት አመት በእቅድ የተያዙ የተለያዩ የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ስራዎች በተመደበላቸዉ የሰዉ ሃይል ፤በጀትና ጊዜ እንዲተገበሩ በርካታ ጥረቶች በክልሉ ሴክሬታሪያትና በሌሎች አከላት ተደርገዋል፡፡
በበጀት አመቱ የሕብረተሰቡን ሁለንተናዊ አቅም በማሳደግና የአመራር ብቃትን ከፍ በማድረግ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ሁሉም አከላት የሥራቸዉ አንዱ አከል አድርገዉ እንዲቀሳቀሱ ከፍተኛ ሥራ የተከናወነ ሲሆን በተለይ የመንግስት መ/ቤቶች ገንዘብ እንዲመደብ በማድረግ የቴክኒክ ዕገዛዎች ተደርገዋል፡፡

ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር ዘመቻ ዋነኛው ተግባር በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎትን ማስፋፋት ፤ ቫይረሱን ከእናት ወደልጅ መተላለፍ ለመከላከል ማለትም የማኅበረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግና አገልግሎቱን ማስፋፋት በእርግዝና ወቅት ምርመራ አድርገው ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ለተገኘባቸው እናቶች ቫይረሱ ወደ ጽንሱ/ልጁ እንዳይተላለፍ ለመከላከል የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ድጋፍና እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው እንዲያገኙ ማድረግ እንዲሁም የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መድሃኒት ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሁሉ በነፃ ማዳረስ በበጀት አመቱ የተከናወኑ ተግባራት ናቸው ፡፡

በድጋፍና እንክብካቤ ስራዎች ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሠዎች ማኅበራትን በማጠናከር በእነርሱ ስር የታቀፉ አባላት እንዲሁም አሣዳጊ ያጡ ሕፃናትን መሠረታዊ ፍላጎታቸውን መሠረት ያደረገ ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

ከተባበሩት መንግስታት የልማት ኘሮግራም (UNDP)፣ ከዩኒሴፍ፣ ከወርልድ ቪዥን፣ ከሲዳ፣ ከመንግስትና ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ የማኅበረሰብ ውይይት ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር ስራ ውስጥ እንዲካተት በማድረግ ከፍተኛና ዉጤታማ ሥራ ተፈፅሟል፡፡

የተለያዩ የዩኤን ድርጅቶች ኤች አይ ቪ/ኤድስ በመከላከልና በመቆጣጠር እረገድ እያደረጉ ያለውን እንቅስቃሴ አንድ ላይ በማቀናጀት የጋራ/ጥምር ዕቅድ በክልሉ በሚገኙ አምስት ወረዳዎች

ማለትም /ቃሉ ፣ ደ/ማርቆስ ከተማ አስተዳደር፣ ይልማና ዴንሳ፣ ደ/ብርሃን እና ደሴ ከተማ / የሙከራ ስራ ለማከናወን የጤና ቢሮ፣የወጣቶችና ስፖርት፣የክልሉና የየወረዳዎቹ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤቶች፣የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣የየወረዳዎቹ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ማህበራት ተጠሪዎች የግብርናና ትምህርት ቢሮ ተሳታፊዎች በተገኙበት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

የክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት በቀጣይ ዘርፈ ብዙ የሆነውን የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምላሽ የማስተባበርና የማቀናጀት ስራው የተሳካ ይሆን ዘንድ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማለትም ከ1998 - 2002 ዓ.ም ድረስ የሚጠቀምበት ስትራቴጂክ ዕቅድ አዘጋጅቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ይህንንም ስትራቴጂክ ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገው ወጪ ብር 1.7 ቢሊዮን እንደሚሆን የተገመተ ሲሆን የክልሉ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት፣ ሴክሬታሪያቱም በማስተባበር፣ ሃብት በማፈላለግና አፈፃፀሙን መከታተል፣ ፈፃሚ አካላት አጋር ድርጅቶችና ህብረተሰቡ ጉልህ ተሳትፎና ምላሽ መስጠት እንደሚጠበቅባቸው ተጠቁሟል ፡፡

# 1. የዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም

## 1.1. መከላከል

ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከሉ ረገድ በ1998 በጀት አመት በክልሉ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የመረጃ ትምህርትና ስርፀት፣ የመረጃ ትምህርት ቁሳቁስ ስርጭት የኮንዶም ስርጭትና አጠቃቀም፣ የአባላዘር በሽታዎችን መከላከልና ህክምና፣ በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የምክርና የደም ምርመራ እንዲሁም ከእናት ወደ ልጅ የቫይረሱን መተላለፍ መከላከል ይገኙበታል።

### 1.1.1. የመረጃ ትምህርትና ስርፀት እንዲሁም ቁሳቁስ ስርጭት

የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭትን በመከላከልና መቆጣጠር ተግባር ውስጥ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ በዘላቂነት መስራት ያለበት ስራ ነው። በመሆኑም በበጀት አመቱ የክልሉን ህብረተሰብ ግንዛቤ ለማሳደግ በበርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተከናዉነዋል።

በክልሉ በሁሉም ዞኖች የኤች አይ ቪ/ኤድስን መተላለፊዎችና መከላከያ መንገዶች፣ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክክርና የደም ምርመራ አገልግሎት ጠቀሜታ፣ ስለድጋፌና እንክብካቤ፣ ስለአድልኦና መገለል፣ የኮንዶም ማስተዋወቅ፣ ስለፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መድሃኒት አጠቃቀም፣ ከእናት ወደ ልጅ የቫይረሱን መተላለፍ ለመከላከል መደረግ ስላለበት ጥንቃቄ ወዘተ ርዕሶች ላይ በተለያዩ ዘዴዎች ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ጥረት ተደርጓል።

በዚህም መሰረት በ1998 የበጀት አመት ለ12584448 ሰዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ የፀረ-ኤድስ ትምህርት ለመስጠት ታስቦ 12398392 ያህል ሰዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት አግኝተዋል። ይህም የዕቅዱን 99% መከናዎኑን ያመለክታል።

በገጠሩ ህ/ሰብ እየተስፋፋ ያለዉን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት ለመቀነስ በገጠሩ ህ/ሰብና በተለይም ሴቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንቅስቃሴ ተደርጎአል።

የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት (ሠንጠረዥ-1)

| ተቁ | ዞን | መለኪያ | የ 1998 በጀት አመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | እቅድ | ክንውን | % |
| 1 | ሰ/ወሎ | በቁጥር | 1082427 | 773176 | 71.43 |
| 2 | አዊ | " | 786268 | 686743 | 87.34 |
| 3 | ሰ/ጎንደር | " | 1,860,000 | 1,800,000 | 96.77 |
| 4 | ኦሮሚያ | " | 477000 | 381923 | 89.14 |
| 5 | ባሕር ዳር | " | 500000 | 673699 | 134.74 |
| 6 | ምዕ/ጎጃም | " | 2350137 | 2467800 | 105.01 |
| 7 | ምስ/ጎጃም | " | 1406984 | 1414720 | 100.55 |
| 8 | ዋግኸምራ | " | 166604 | 254403 | 152.70 |
| 9 | ደ/ወሎ | " | 889724 | 599481 | 67.38 |
| 10 | ሰ/ሸዋ | " | 1200000 | 1375963 | 114.66 |
| 11 | ደ/ጎንደር | " | 1864304 | 1970484 | 105.70 |
| | ድምር | " | 12584448 | 12398392 | 99.33 |

## በክልል ደረጃ የመረጃ ትምህርት ቁሳቁስ ስርጭት(ሠንጠረዥ2)

| ተቁ | የመረጃ ትምህርት ቁሳቁስ አይነት | መለኪያ | ፊዚካል ሥራ | | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | % | |
| 1 | የተሰራጩ የማስተማሪያ ቪዲዮ ካሴት | ቁጥር | 120 | 125 | 104 | |
| 2 | የማስተማሪያ ሲዲዎች | » | 120 | 115 | 95 | |
| 3 | በራሪ ጽሑፍ | » | 65000 | 71500 | 110 | |
| 4 | ለኤግዚብሽን ዝግጅት ቻርትና ፎቶ ግራፍ | » | 75 | 214 | 265 | |
| 5 | በተለያዩ መፅሔቶች ላይ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መልዕክቶች እንዲታተሙ ማድረግ | » | 3 | 4 | 133 | |
| 6 | ለመገናኛ ብዙኃን ስለ ክልሉ ኤች አይቪ ኤድስ ወቅታዊ መግለጫ መስጠት | » | 4 | 4 | 100 | |
| 7 | በመገናኛ ብዙኃን ስለ ክልሉ ሀቶቨሐጀዐድስ በበዓላት ወቅት መልዕክት ማስተላፏ | » | 3 | 3 | 100 | |
| 8 | ፖስተር ማሳተም | » | 70000 | 70000 | 100 | |
| 9 | ቲ- ሸርት በማሳተም ማሰራጨት | » | 7000 | 7000 | 100 | |
| 10 | በባነር መልዕክቶች ማስተላለፍ | » | 12 | 23 | 192 | |
| 11 | የድህረ ገፅ መረጃዎችን ወቅታዊ ማድረግ | » | 1 | 1 | 100 | |
| 12 | የአቅል መፅሄትን በማሳተም ማሰራጨት | » | 3500 | 3900 | 114 | |

| የ 1998 በጀት አመትየመረጃ ቁሳቁሶች ሥርጭት መጠን በዞን ደረጃ (ሠንጠረዥ-3) | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተቁ | ዞን | መለኪያ | እቅድ | ክንውን | % |
| 1 | ሰ/ወሎ | በቁጥር | 56261 | 33678 | 59.86 |
| 2 | አዊ | " | 208072 | 75975 | 36.51 |
| 3 | ሰ/ጎንደር | " | 654,440 | 259,191 | 39.61 |
| 4 | ኦሮሚያ | " | 80769 | 24900 | 30.83 |
| 5 | ባሕር ዳር | " | 180000 | 655900 | 364.39 |
| *6* | *ምዕ/ጎጃም* | *"* | *285108* | *230746* | *80.93* |
| 7 | ምስ/ጎጃም | " | 558014 | 329071 | 58.97 |
| 8 | ዋግኽምራ | " | 68647 | 41503 | 60.46 |
| 9 | ደ/ወሎ | " | 115406 | 94113 | 81.55 |
| 10 | ሰ/ሸዋ | " | 86400 | 134660 | 155.86 |
| 11 | ደ/ጎንደር | " | 750000 | 187666 | 25.02 |
| | ድምር | | 3043117 | 2067403 | 67.99 |

### 1.1.2. የኮንዶም ስርጭት

በክልሉ የኮንደም አጠቃቀምና ስርጭት ከአመት አመት እየጨመረ ይገኛል፡፡ በ1998 የበጀት አመት በክልሉ 10500937 ኮንዶችም ለማሰራጨት ታቅዶ 10282559 የተሰራጩ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ በዲ.ኬ.ቲ ኢትዮጵያ በክልሉ 9034220 ኮንዶሞች እንደተሠራጩ በሪፖርት ተገልፆልናል፡፡ የዲ.ኬ.ቲ ጽ/ቤቶች በሁሉም ዞኖች ባለመኖሩና በዲ.ኬ.ቲ የተሰራጨዉን የኮንዶም ስርጭት መረጃ ዞኖቹ በትክክል ማግኘት ባለመቻላቸዉ የመረጃ ልዩነት ተፈሮአል፡፡ ከዚህ ሪፖርት እንደምረዳዉ የኮንዶም ስርጭት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደመጣና ምንም እንኩዋን በጥናት የሚመለስ ቢሆንም በኮንዶም አጠቃቀም ላይ የባህርይ ለዉጥ እንደመጣ ያመለክታል፡፡

የ1998 በጀት አመት ኮንዶም ስርጭት መጠን በዞን ደረጃ (ሠንጠረዥ-4)

| ተቁ | ዞን | መለኪያ | የ1998 የበጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | እቅድ | ክንውን | % |
| 1 | ሰ/ወሎ | በቁጥር | 210234 | 170167 | 80.94 |
| 2 | አዊ | " | 136680 | 42908 | 31.39 |
| 3 | ሰ/ጎንደር | " | 1068000 | 825267 | 77.27 |
| 4 | ኦሮሚያ | " | 202044 | 104593 | 51.77 |
| 5 | ባሕር ዳር | " | 900000 | 913598 | 101.51 |
| 6 | ምዕ/ጎጃም | " | 330938 | 408742 | 123.51 |
| 7 | ምስ/ጎጃም | " | 398267 | 247840 | 62.23 |
| 8 | ዋግኽምራ | " | 166500 | 97931 | 58.82 |
| 9 | ደ/ወሎ | " | 620693 | 536592 | 86.45 |
| 10 | ሰ/ሸዋ | " | 600000 | 395986 | 66.00 |
| 11 | ደ/ጎንደር | " | 580000 | 282560 | 48.72 |
| | በክልል ደረጃ | | 5213356 | 4026184 | 77.23 |

### 1.1.3. የአባላዘር በሽታዎች ቁጥጥር

የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭትን ከሚያባብሱት ጉዳዮች ዋነኛው የአባላዘር በሽታዎች በመሆናቸው በ1998 የበጀት አመት ለ 49939 ሰዎች ህክምና ለመስጠት ታቅዶ 29555 ሰዎች ህክምና አግኝተዋል፡፡ በየዓመቱ ከሚደረጉት ሪፖርቶች እንደምንረዳዉ የአባለዘር በሽታዎች ስርጭት እየቀነሰ መሆኑን ማዬት ተችሎአል ፡፡ ነገር ግን የመቀነሱ ምክንያት በሪፖርር አደራረግ ችግር ይሁን ወይም ደግሞ በትክክል የሽታዉ ስርጭት መቀነሱ መሆኑ ወደፊት በጥናት የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡

የአባላዘር በሽታ ሕክምና መስጠት (ሠንጠረዥ 5)

| ተቁ | ዞን | መለኪያ | የ1998 የበጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | እቅድ | ክንውን | % |
| 1 | ሰ/ወሎ | በቁጥር | 4775 | 2806 | 58.76 |
| 2 | አዊ | " | 1560 | 619 | 39.68 |
| 3 | ሰ/ጎንደር | " | 10170 | 5013 | 49.29 |
| 4 | ኦሮሚያ | " | 1966 | 611 | 31.08 |
| 5 | ባሕር ዳር | " | 1500 | 1110 | 74.00 |
| 6 | ምዕ/ጎጃም | " | 1856 | 1871 | 100.81 |
| 7 | ምስ/ጎጃም | " | 6514 | 5037 | 77.33 |
| 8 | ዋግኽምራ | " | 3238 | 592 | 18.28 |
| 9 | ደ/ወሎ | " | 7360 | 6938 | 94.27 |
| 10 | ሰ/ሸዋ | " | 6000 | 3216 | 53.60 |
| 11 | ደ/ጎንደር | " | 5000 | 1742 | 34.84 |
| | በክልል ደረጃ | | 49939 | 29555 | 59.18 |

### 1.1.4. በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረት የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት

የኤች አይ ቪ ን ስርጭት ለመግታት በሚደረገው እንቅስቃሴ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ምክርና የደም ምርመራ ዋነኛ የመከላከያ ዘዴ በመሆኑ በክልሉ አገልግሎቱን ለማስፋፋት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።በመሆኑም በክልላችን የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት መስጫ ተቐማት ቀደም ብለዉ ከነበሩት አነስተኛ ቁጥር ወደ 152 ከፍ እንዲል ተደርጎአል። ከነዚህም ዉስጥ 142 የመንግስት፣4 መንግስታዊ ያልሆኑ እንዲሁም 6 የግል ድርጅቶች ይገኙበታል። በዚህም መሠረት በበጀት አመቱ በክልሉ ያሉት የምክርና የምርመራ አገለግሎት መስጫ ተቋማት በሆስፒታሎች ያሉትን ጨምሮ 152 ደርሷል። በ1998 የበጀት አመት ውስጥም በነዚህ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ለ ሰዎች አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 128619 ያህል ሰዎች አገልግለቱን አግኝተዋል። ካለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር አፈፃፀሙ በ32483 ሰዎች ብልጫ አሳይቷል። ጭማሪውም በፐርሰንት 38% ሆኖ እናገኘዋለን።

የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት ካገኙት ሰዎች ውስጥ 15.9% ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ተገኝቷል ።

በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና ደም ምርመራ አገልግሎት በዞን ደረጃ (ሠንጠረዥ 6)

| ተቁ | ዞን | መለኪያ | የ 1998 በጀት አመት | | | ቫይረሱ ተገኘባቸዉ ሰዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | እቅድ | ክንውን | % | ወ | ሴ | ድምር |
| 1 | ሰ/ወሎ | በቁጥር | 22013 | 10286 | 46.73 | 1050 | 807 | 1857 |
| 2 | አዊ | " | 8420 | 4280 | 50.83 | 146 | 241 | 387 |
| 3 | ሰ/ጎንደር | " | 23,515 | 20,846 | 88.65 | 1801 | 2081 | 3882 |
| 4 | ኦሮሚያ | " | 4200 | 3414 | 35.31 | 119 | 174 | 293 |
| 5 | ባሕር ዳር | " | 17500 | 10835 | 61.91 | 1165 | 1354 | 2519 |
| 6 | ምዕ/ጎጃም | " | 8874 | 5841 | 59.14 | 296 | 313 | 599 |
| 7 | ምስ/ጎጃም | " | 14525 | 9059 | 62.37 | 597 | 742 | 1339 |
| 8 | ዋግኽምራ | " | 4000 | 658 | 16.45 | 65 | 86 | 151 |
| 9 | ደ/ወሎ | " | 58000 | 39549 | 68.19 | 2882 | 3126 | 6008 |
| 10 | ሰ/ሸዋ | " | 38000 | 14896 | 39.20 | 804 | 1904 | 2706 |
| 11 | ደ/ጎንደር | " | 12000 | 8855 | 73.79 | 587 | 656 | 1243 |
| | ድምር | " | 211047 | 128619 | 61.57 | 90502 | 11482 | 20984 |

በ1998 በጀት አመት በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የደም ምርመራ አገልገሎት ከአለፉት አመታት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የሆነ የአፈፃፀም ዕድገት መመዝገቡን መረጃዎች ይጠቁማሉ ። ከክልሉ የህዝብ ብዛት አንፃር ሲመዘን የተመዘገበዉ ዉጠ ት አነስተኛ ቢመስልም ከተፈጠረዉ የባህሪ ለዉጥ አንፃር ሲታይ ደግሞ አፈጻፀሙ ከፍተኛ ነዉ ።

### 1.1.5 ደህንነቱ የተጠበቀ የደም አቅርቦት

በ1998 የበጀት አመት ደህንነቱ የተጠበቀ የደም አቅርቦት ለማከሄድ በተደረገዉ ጥረት በ4 ሆስፒታሎች( ባህር ዳር፣ በጎንደር፣በደሴና ደ/ታቦር) 4599 ሰዎች የደም ልገሳ አድረገዉ 3.8 በመቶዉ ቫይረሱ ተገኝቶባቸዋል።

### 1.1.6 ከእናት ወደ ልጅ የቫይረሱን መተላለፍ መከላከል

በክልሉ በ34 የጤና ድርጅቶች የኤች አይ ቪ ቫይረስ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል ጥረት እየተደረገ ይገኛል:: በዚህም መሠረት 10393 ያህል እናቶች የምክር የአገልግሎቱ ተጠቃማዎች ሆነዋል:: አፈፃፀሙ ከአለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ4394 ቁጥር ብልጫ አሳይቷል:: አገልግሎቱን ካገኙት መካከል 5231 የደም ምርመራ ያደረጉ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 403 ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ተገኝቷል:: ቫይረሱ ከተገኘባቸው ውስጥ 242 እናቶችና 126 ሕፃናት የመከላከያ መድሃኒት አግኝተዋል::

የቫይረሱን ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለመከላከል የምክር አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ እናቶች (ሠንጠረዥ 7-)

| ተቁ | ዞን | መለኪያ | የ1998 የበጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | እቅድ | ክንውን | % |
| 1 | ሰ/ወሎ | በቁጥር | 1215 | 727 | 60 |
| 2 | አዊ | " | - | - | - |
| 3 | ሰ/ጎንደር | " | 1181 | 2038 | 172 |
| 4 | ኦሮሚያ | " | 49 | 258 | 59 |
| 5 | ባሕር ዳር | " | 1200 | 1305 | 109 |
| 6 | ምዕ/ጎጃም | " | 1250 | 773 | 62 |
| 7 | ምስ/ጎጃም | " | 1250 | 610 | 49 |
| 8 | ዋግኽምራ | " | - | 88 | - |
| 9 | ደ/ወሎ | " | 5003 | 2264 | 45 |
| 10 | ሰ/ሸዋ | " | 1750 | 272 | 15. |
| 11 | ደ/ጎንደር | " | 450 | 1698 | 377 |
| | ድምር | | 13348 | 10033 | 75 |

## 2. ድጋፍና እንክብካቤ

### 2.1 ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ፣ ወላጆቻቸውን ያጡና ተጋላጭ ህፃናትና ልጆች

ኤች አይ ቪ/ኤድስ እያደረሰ ያለውን የማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና የስነ-ልቦና ጉዳት ለመቀነስ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ተግባራት አንዱ ድጋፍና እንክብካቤ በመሆኑ በክልሉም በስፋት እየተሰራበት ይገኛል፡፡

በኤች አይ ቪ/ኤድስ ተጠቂ የሆኑትን ሰዎችና ከዚሁ ጋር በተያያዘ ወላጆቻቸውን ያጡ እንዲሁም ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትና ልጆችን መሠረታዊና ዘላቂነት ያላቸው የድጋፍ አይነቶችን በበርካታ ፈፃሚ ድርጅቶች አማካኝነት እንዲደርሳቸው ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በበጀት አመቱ ለ8485 ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችና 44277 ወላጆቻቸውን በኤድስ ምክንያት ላጡና ተጋላጭ ለሆኑ ህፃናት መሠረታዊ ፍላጐታቸውን በማሟላት፣የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ፣ የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ እንዲያካሂዱ እገዛ በማድረግ፣ የቤት ለቤት እንክብካቤ በማድረግ፣ የተደራጁ ማህበራትን የሰው ሃይልና የማቴሪያል እገዛ በማድረግ ... ወዘተ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸዉን ከማሙዋላት ባሻገር ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሠዎችና ወላጆቻቸዉን ያጡ ህፃናት በዘላቂነት እራሳቸዉን ሊያስተዳድሩበት በሚያስችላቸዉ ልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ተግባራት እንዲሰማሩ ተደርጎአል፡፡ ከገቢ ማስገኛ ስራዎች ዉስጥም የዳቦ መጋገሪያ፣የበግና የፍየል እርባታና ማድለብ፣የወተት ላም እርባታ፣የዶሮ እርባታ፣የከብት ማድለብ፣የሐር ትል፣በጉዋሮ አትክልት፣በትራንስፖርት ዘርፍ (ጋሪ፣ሞተር ብስክሌት፣ሚኒባስ)፣መብራት በሌለባቸዉ ወረዳወች ጀኔሬተር፣ሻወር፣ስቴሽነሪና ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ሊስትሮ (4000 ቁጠባ)፣በርካታ የሽቀጣሽቀጥ ሱቆች፣ፀጉር ቤት፣ቴሌ ሴንተር…ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡

የገቢ ማስገኛ ስራዎች ዉጤታማ እንዲሆኑ  በልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ ሥልጠና ተሠጥቶአል፡፡

በገቢ ማስገኛ ስራዎች በመሰማራታቸዉ የተረጅነት ስሜት እየቀነሰ መምጣቱ፣በማህበር በስፋት መደራጀታዉ፣የስነልቦና መረጋጋት መፈጠሩ፣በስራቸዉ ወላጆቻቸዉን ያጡ ህፃናትን ይዘዉ በመንከበከብ ላይ መሆኑ፣ ትርፋማ በመሆን ነሮአቸዉን በተሻለ ደረጃ እየመሩ መሆኑ …ወዘተ

የታዩና ሊጠናከሩ የሚገባቸዉ ለዉጦች ናቸዉ፡፡ ይህ ጅምር እየተደረገ ያለዉን የድህነት ቅነሳ ፕሮገራም የሚደግፍ በመሆኑ ወደፊት ተጠናክሮ የቀጥላል፡፡

በተጨማሪም የአለም የምግብ ፕሮግራም በባ/ዳር፣ በደሴ፣በጎንደርና በደብረብርሃን ለ3524 ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች፣ ለ9112 ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት እና ለ146 ቤት ለቤት ተንከባካቢዎች ወርሃዊ የምግብ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጅቱን አጠናቅቋል፡፡ ተጠቃሚዎችም በዕድሮችና የሚመረጡ ሲሆን አስፈፃሚ አካላትም ተስፋ ጎህ ማኀበርና ኦሳ ይሆናሉ፡፡

ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ማህበራት ቁጥር መበራከትና *ከ10 ወደ 75* ከፍ ማለቱና በዉስጣቸዉም 8485 አባላትን በማካተት በመከላከሉ፣በድጋፍና እንክብካቤ ስራዎች ላይ ተሠማርተዉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ የክልሉ ሴክሬታሪያትም ለነዚህ ማህበራት አቅም ለማጎልበት ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር በቅንጅት በገንዘብ፣በሠዉ ሃይልና በቁሳቁስ እንዲጠናከሩ ተደርጎአል፡፡

የድጋፍና እንክብንቤ አገልግሎት ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት በዞን ደረጃ
(ሠንጠረዥ 8)

| ተቁ | ዞን | መለኪያ | የ1998 የበጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | እቅድ | ክንውን | % |
| 1 | ሰ/ወሎ | በቁጥ | 2414 | 3451 | 126.38 |
| 2 | አዊ | " | 1715 | 2954 | 172.24 |
| 3 | ሰ/ጎንደር | " | 4348 | 4900 | 112.70 |
| 4 | ኦሮሚያ | " | 2489 | 4426 | 177.82 |
| 5 | ባሕር ዳር | " | 3000 | 4715 | 157.17 |
| 6 | ምዕ/ጎጃም | " | 2501 | 3811 | 152.38 |
| 7 | ምስ/ጎጃም | " | 2906 | 3854 | 122.30 |
| 8 | ዋግኽምራ | " | 1246 | 838 | 67.26 |
| 9 | ደ/ወሎ | " | 4848 | 5955 | 122.83 |
| 10 | ሰ/ሸዋ | " | 3201 | 5883 | 183.79 |
| 11 | ደ/ጎንደር | " | 2900 | 3486 | 120.21 |
| | ድምር | | 31568 | 44277 | 140.84 |

ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች የተደረገ ድጋፍና እንክብካቤ (ሠንጠረዥ 9)

| ተቁ | ዞን | መለኪያ | የ1998 የበጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | እቅድ | ክንውን | % |
| 1 | ሰ/ወሎ | በቁጥር | 603 | 526 | 87.23 |
| 2 | አዊ | " | 858 | 416 | 48.48 |
| 3 | ሰ/ጎንደር | " | 1865 | 2343 | 125.63 |
| 4 | ኦሮሚያ | " | 450 | 104 | 23.11 |
| 5 | ባሕር ዳር | " | 800 | 967 | 120.88 |
| 6 | ምዕ/ጎጃም | " | 537 | 633 | 118 |
| 7 | ምስ/ጎጃም | " | 500 | 495 | 96 |
| 8 | ዋግኽምራ | " | 100 | 111 | 111.00 |
| 9 | ደ/ወሎ | " | 1956 | 1886 | 96.42 |
| 10 | ሰ/ሸዋ | " | 500 | 645 | 129.00 |
| 11 | ደ/ጎንደር | " | 560 | 659 | 117.68 |
| | ድምር | | 8729 | 8785 | 859.43 |

### 2.2 የቤት ለቤት እንክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ስልጠናዎች

የቤት ለቤት እንክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ስልጠና በኩልም ለ1419ሰዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 1247 ሰዎች ስልጠናው ተሠጥቷል፡፡ የዕቅዱ 87.8% ተፈጽሟል፡፡ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች የተጠናከረና ቀጣይነት ያለው የቤት ለቤት እንክብካቤ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያስችል ስልጠና በመሆኑ በቀጣይም ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ማህበርና በሌሎች አካላት ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡

በክልሉ ሴክሬታሪያት፣ በኤፍ ኤች አይ እና በኦሳ ትብብር በባሕር ዳር፣ ጎንደርና ደሴ ከተሞች አልጋ ላይ ለዋሉ 1012 ሕሙማን የሚሠጠው የቤት ለቤት እንክብካቤ አገለግሎት በአርያነቱ ተጠቃሽ ነው፡፡

### 2.3 የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ህክምና

መንግስት የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት በነፃ በማቅረቡ፣በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት እየተስፋፋ በመምጣቱ እንዲሁም ከዚህ ቀደም የነበረው አድልኦና መገለል የግንዛቤ ሁኔታ መሻሻል በማሳየቱ የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በ1998 የበጀት አመት 8742 ሰዎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የነበሩ ሲሆን የወሰኑ ሰዎች በመሞታቸዉና በማቋረጣቸዉ 6974 ሰዎች ብቻ እስከ

በጀት አመቱ መጨረሻ ተጠቃሚ ሆነዋል።ይሁን እንጅ በክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ለ1998 ከተያዘዉ ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር የተጠቃሚዎች ቁጥር አነስተኛ እንደሆነ ለመረዳት ተችሎአል። ለዚህም እንደምክንያት የሚጠቀሰዉ አገልግሎቱ በተወሰኑ ተቋማት ብቻ መሰጠቱ፣ በከፍተኛ የጠ ₃ና ባለሞያዎች ብቻ አገልግሎቱ መሰጠት መጀመሩ ቅስቀሳዉ በስፋት አለመደረጉ፣በመድሃኒቱ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶች መኖርና አሁንም ማግለልና መድሎዉ ይደርስብናል በሚል ፍርሃት የተጠቃሚዎችን ቁጥር አነስተኛ ካደረጉት ምክናያቶች ትቂቶቹ ናቸዉ።

**3. <u>የአቅም ግንባታ ሥራዎች</u>**

የክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክሬታሪያት ወረርሽኙን ለመከላከል ትኩረት ሰጥቶ ከሚተገብራቸው ሥራዎች የአቅም ግንባታ ሥራ አንዱ ቁልፍ ተግባር ነው።

በ1998 የበጀት ዓመት ከተለያዩ ረጅ ድርጅቶች የሚገኘውን በጀት ውጤታማ በሆኑ ተግባራት ላይ ለማዋል ለተለያዩ ፈፃሚ አካላት የተለያዩ የመፈፀም አቅም ማጠናከሪያ ስልጠናዎች ተሠጥተዋል። ሥልጠናዎች በዕቅድ እየተደገፉ በክልል በዞንና በወረዳ ደረጃ ተተግብረዋል።

በ1998 የበጀት አመት በዕቅድ ተይዘው ከተከናወኑት ዋና ዋና የሥልጠና አይነቶች መካከል :-

- የማህበረሰብ ውይይት
- የሜይንስትሪሚግ
- የገቢ ማስገኛ
- የቤት ለቤት እንክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ
- የሕይወት ክህሎት
- የፕሮጀክት ዝግጅት ወዘተ በግንባር ቀደምት ይጠቀሳሉ።በበጀት አመቱ መጨረሻ አከበቢ ኢምፓክት ከሚባል አገር በቀል ድርጀት በተገኘ የበጀት ድጋፍ ለ86 ክልል የዞንና ወረዳ ባለሞያዎች 12 ቀን የፕሮጀክት ዝግጅት ስልጠና የተሠጠ ሲሆን ከሰልጣኛች መከከልመ 7 ሰ ₃ቶች ነበሩ ። በበጀት አመቱ በተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጀት በኩል የማህበረሰብ ዉይይትን የበለጠ ለማጠነከር ታስቦ ለ19 ሰዎችም የሥራ አመራር ስልጠና በ3 ዙር ተሰጥ±ል ። ለ12 ሰዎች ክልል አቀፍ የአመራር የአሰልጣኞች ስልጠና በበጀት አመቱ በ6 ዙር ተሰጥ±ል ።

**1998 በጀት አመት በተለያዩ አከላት ታቅደዉ የተፈፀሙ የስልጠና አይነቶች (ሠንጠረዥ 10)**

| ተቁ | የሥራ ዝርዝር | መለኪያ | የ 1998 በጀት አመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | እቅድ | ክንውን | % |
| 1 | የቤት ለቤት እንክብንቤ አሰጣት ስልጠና | በቁጥር | 1227 | 1450 | 118.17 |
| 2 | የአቻ ለአች ትምህርት ስልጠና | ″ | 1952 | 9252 | 473.98 |
| 3 | የገቢ መስገኛ ሥራ ስልጠና | " | 2432 | 732 | 30.10 |
| 4 | የሕይወት ክህሎት ስልጠና | " | 3421 | 5984 | 174.92 |
| 5 | የሜይንስትሪሚንግ ስልጠና | " | 918 | 695 | 75.71 |
| 6 | የማህበረሰብ ወይይት ስልጠና | " | 4164 | 3831 | 78.51 |
| 7 | የባህሪ ለዉጥ ስርፀት ስልጠና | " | 2286 | 6345 | 277.56 |
| 8 | የፕሮጄክት ዝግጅትና አሰተዳዳር ስልጠና | | 602 | 86 | 14.29 |
| | ድምር | " | 17002 | 28375 | 166.89 |

### 3.1 የማህበረሰብ ውይይት

በሃገር አቀፍ ደረጃ የወጣዉን የኤች.አይ.ቪ/አድስ ስትራቴጅና የህዝብ ማቀጣጠያ ሰነድ መስፈፀሚያ ስልት የሆነዉ የማህበረሰብ ዉይይት በክልላችን በ47 ወረዳዎች ዉስጥ በ441 ጣቢያዎች ተጀምሮ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በነዚህ ጣቢያዎችም ከ31000 በላይ ተሳታፊ ይገኛል፡፡ ይህ ፕሮገራም በክልላችንም ሆነ በሌሎች ክልሎች እንደተሞከረዉ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በባህላዊ ጉዳዮች ላይ በመወያትና ችግሮችን በመለየት አካባቢያዊ መፍትሄ በመስጠት ለምናካሂደዉ የልማት እንቅስቃሴ ዉጤታማ ፕሮግራም እንደሆነ ተረጋግጦአል፡፡

በ1998 በክልሉ የማህበረሰብ ውይይት ተጀምሮ በሚካሄድባቸው 47 ወረዳዎች ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ከፍተኛ የሆነ የባሕሪ ለውጥ አመላካች ሁኔታዎች ተፈጥሯል፡፡ ማህበረሰቡ በሚያደርጋቸው የፀረ ኤድስ ሥራ ዉይይቶች ከፍተኛ የሆኑ በባሕሪ ለውጥ አመለካከቶች ተመዝግበዋል፡፡ ለአብነትም ያህል፡-

- በርካታ የተሳሳቱ አመለካከቶች ተለይተዋል
- በብዙ ቦታዎች ያለቅድመ ምርመራ ጋብቻ እንዳይፈፀም ዉሳኔ ላይ መድረስና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ

- የማግለልና መድሎ ድርጊቶች እንዲቀንሱ አስተዋፅኦ ማድረጉ
- በአካባቢ ሃብት የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎት ለተለያዩ ወገኖች መስጠት መጀመሩ
- የኤች አይ ቪ ጉዳይ ሕብረተሰቡ የሚመለከተው መሆኑን ማመኑና የተጠናከረ ቀጣይነት ያለው ጥረት ማድረግ መጀመሩ
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በዘላቂነት ለመከላከል በማህበር መደራጀታቸዉ
- የጤና አገልግሎቶች ተጠቃሚ ቁጥር እንዲጨምር ማድረጉ(VCT,ART,PMTCT,STIs)
- በኮንዶም ላይ የነበረዉ የተሳሳተ አመለካከት እየቀነሰ መምጣቱ
- ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዲቀረፍ ጥረት መደረጉ
    - የሴት ልጅ ግርዛት
    - ያለዕድሜ ጋብቻ
    - ውርስና ዋርሳ
    - ቅምጥ
- በስነ ወሲብ ዙሪያ በግልፅ ውይይት መጀመሩ ወዘተ... የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በዚህም መሠረት ይህን ፕሮግራም በክልሉ ዉስጥ ባሉ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ለማስፋፋት የአብክመ ኤች አይቪ ኤድስ መከ/መከ ሴክሬታሪያት ፣ከክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮና ከተባበሩት መንግስታት የልማት ኘሮግራም ጋር በመተባበር ለ317 የተለያዩ ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ለ3524 የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የአመቻቾች ስልጠና ተሠጥቷል፡፡

ይሁን እንጅ ይህን ፕሮግራም በስፋት ለማካሄድ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ቃል የገቡልን ድርጅቶች በጀቱን ሊለቁ ባለመቻላቸዉ ማካሄድ አልተቻለም፡፡ ሆኖም ግን በተወሰኑ ወረዳዎች ከመንግስት መደበኛ በጀት በመጠቀም ፕሮገራሙ ተጀምሮአል፡፡

ካመጣዉ ዉጤት አንፃር በሚቀጥሉት ዓመታትም ይህን ፕሮግራም አጠናክሮ ለመቀጠል ሴክሬታሪያቱ በጀት ከተለያዩ ረድዔት ድርጅቶች እያፈላለገ ቢሆንም በአካባቢ ሃብትና ከመንግስት መደበኛ በጀት መታገዝ ያለበት በመሆኑ የክልሉ መንግስት ከወዲሁ ትኩረት ሰጥቶ በጀት ሊመድብ ይገባዋል፡፡

**የአሰልጣኞችና የአመቻቾች ስልጠና ተሳታፊዎች ብዛት ( ሠንጠረዥ 11)**

| የስልጠና አይነቶች | የሥልጠና ቦታዎች | የሠልጣኝ ብዛት | | | የፋይናንስ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | **ዕቅድ** | **ክንውን** | % | **ዕቅድ** | **ክንውን** | % |
| የአሠልጣኞች ስልጠ | **ባሕር ዳር** | 185 | 190 | 103 | 331490.00 | 304260.06 | 92. |
| | **ደሴ** | 138 | 127 | 92 | 259103.00 | 163219.33 | 63 |
| | **1.ንዑስ ድምር** | **323** | **317** | **98** | **590593.00** | **467479.39** | **79** |
| የአመቻቾች ስልጠና | **ጐንደር** | 634 | 633 | 99.8 | 331604.00 | 216671.60 | 66 |
| | **ደ/ታቦር** | 381 | 380 | 99.7 | 211815.00 | 136529.00 | 64 |
| | **ባ/ዳር** | 411 | 411 | 100 | 222941.00 | 139460.00 | 62 |
| | **ደ/ማርቆስ** | 581 | 579 | 99.7 | 309039.00 | 226311.00 | 72 |
| | **ወልዲያ** | 462 | 462 | 100 | 247301.40 | 194861.00 | 78.8 |
| | **ደሴ** | 572 | 560 | 97.9 | 307046.00 | 186181.00 | 61 |
| | **ደ/ብርሃን** | 502 | 499 | 99.4 | 271624.00 | 173699.00 | 64 |
| | **2.ንዑስ ድምር** | **3543** | **3524** | **99.5** | **1901370.4** | **1273712.6** | **68** |
| | **ድምር 1+2** | **3866** | **3831** | **99** | **2491963.40** | **1741191.99** | **70** |
| | የ9ኙ ማሰልጠኛ ተቋማት የጋራ ወጭ | | | | 118857.10 | 118857.10 | 100 |
| | **ጠ/ድምር** | | | | **2610820.5** | **1860049.09** | **71.2** |

## 3.2 ሜይንስትሪሚንግና ፖርትነርሽኘ

### 3.2.1 ሜይንስትሪሚንግ

በ1998 በጀት አመት የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች ካለፉት አመታት በተሻለ መልኩ የተለያዩ የፀረ ኤድስ ተግባራት እንዲፈፀሙ ታስቦ ለሴክተር መ/ቤቶች ተወካዩች የሜይንስትሪሚንግ ስልጠና ተሠጥቷል።

ለ105 ሰዎች የአሰልጣኞች ስልጠና በክል ደረጃ የተሠጠ ሲሆን ተሳታፊዎች ከክልል ከዞንና ከወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች የተመለመሉ ነበሩ። ሥልጠናው ለሴክተር መ/ቤቶች ከፍተኛ አቅም ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል። በዚህም መሠረት በዞኖችና በወረዳዎች በ1998 በጀት አመት ውስጥ የተለያዩ አካላት የፀረ ኤድስ ሥራዎችን ከመደበኛ ሥራቸው ጋር አካተውና ከፍተኛ ትኩረት ሠጥተው እንዳንቀሳቀሱ ለተለያዩ የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶችና ሌሎች አካላት የሜይንስትሪሚንግ ሥልጠና ለ629 ሰዎች ተሠጥቷል። ይህም የዕቅዱን 73.6% መፈፀሙን ያመለክታል።

ከዚህ ሥልጠና ባሻገር የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ተካሄደዋል። ሦስት ኮምፒዮተሮች ተገዝተው ለሦስት ሴክተር መ/ቤቶች ለወባስ፣ ባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ እና ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ/ ተሠጥተዋል።

በክልልም ሆነ በወረዳዎች የተወሰኑ ሴክተሮች ኤድስ ፈንድ እያቋቋሙ ሲሆን በቢሮ ደረጃ 15 ሴክተሮች ሁሉም ባይሆኑም በወረዳዎችና በዞኖች እየተመሠረተ እንደሆነ ለአብነትም በምስ/ጎጃም ዞን በሁሉም ወረዳዎች የተ ቋቋመ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል፡፡

በአጠቃላይ በ1998 የበጀት ዓመት በሴክተር መ/ቤቶች የሚካሄደው የፀረ ኤድስ ተግባራት ሲመዘን የተከናወኑ ተግባራት ዝቅተኛ እንደሆነ ለመገምገም ተችሏል።

የሴክተር መ/ቤቶች የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ የተጠናከረ አለመሆኑን ከሚጠቀሙ ምክንያቶች አንዱ ከሴክሬታሪያቱ በቂ በጀት ለሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች አለመለቀቁ ይጠቀሳል።

ሌላዉ በበጀት ዘመኑ ሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች ከመደበኛ በጀታቸው 2% ለፀረ ኤድስ ሥራ ማስፈፀሚያ እንዲመደቡ በመንግስት በኩል የተገለጸ ቢሆንም ከጥቂት ሴክተር መ/ቤቶች በስተቀር ለጉዳዩ ትልቅ ትኩረት ባለመስጠታቸው የተነሳ የፀረ ኤድስ ሥራዎችን አፈፃፀም ዝቅተኛ አድርጎታል። ስለዚህ በቀጣይ ሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች ከሴክሬታሪያቱ የሚመደበውን በጀት ብቻ ሳይመለከቱ ኤድስ ፈንድ ማቋቋም 2% ከመደበኛ በጀት መድበው ሊንቀሳቀሱ ይገባል። የሴክተር መ/ቤቶች እቅድ አፈፃፀም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል።

### የሴክተር መ/ቤቶች አፈፃፀም (ሠንጠረዥ 12)

| ተ.ቁ | መ/ቤት | ከሴክሬታሪት የተመደበ በጀት | ታቅደው የተፈፀመ ተግባራት | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ጤና ቢሮ | 24,652,166.27 | ♦ ለ141 ጤና ኬላ ግንባታ፣ የጤና ኤክስነንሽን ስልጠና፣ የ3 ቪሲቲ ማዕከላት ግንባታ | ቢሮዉ በቂ ሪፖረት ሊያቀረብ አልቻለም:: |
| 2 | ቱሪዝም ኮሚሽን | - | ♦ ለ50 ወንዶችና ለ 8 ሴቶች በድምሩ ለ58 ሰዎች የፀረ ኤድስ ት/ት ተሠጥቷል<br>♦ ከሠራተኞወ ደመወዝ እየተዋጣ ለ 1 ሴት ሰራተኛ ድጋፍ እየተደረገ ነው<br>♦ ለ2050 ሰዎች በመ/ቤቱ የግንዛቤ ማስጨበጫነት ተሠጥቷል:: | ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሜይንስትሪም በማድረግ በራሳቸው ወጭ የተሰራ |
| 3 | ማህበራዊ ዋስትና | - | ♦ ለመ/ቤቱ 60 ሰራተኞች (ወ- 37 ሴ - 23) የፀረ - ኤድስ ትምህርት ተሠጥቷል::<br>♦ ኤድስ ፈንድ ተቋቁሟል:: | « |
| 4 | ማስታወቂያ ቢሮ | - | ♦ በቪዲዩ የተደገፉ ትምህርት ለ52 ወንድና ለ24 ሰ ፥ት ሰራተኞች ትምህርት ተሠጥቷል::<br>♦ ከሠራተኞች በር 1054 ለተስፋ ጎህ ገቢ ተደርጓል<br>♦ በሬድዮ (ደሴ፣ ጎንደር፣ ደ/ማርቆስ) በአዲስ ዙሪያ ት/ት ተሠጥቷል::<br>♦ የፀረ ኤድስ መልዕክት ያነገቡ የተለያዩ መረጃዎች ለሕ/ሰቡ ተሠራጭተዋል:: | « |
| 5 | ኢንቨስትመንት | 5192.00 | ♦ 132 ብሮሸሮች ተዘጋጅተው ተሠራጭተዋል<br>♦ የኤድስ ፈንድ ተቋቁሞ ብር 1098 ተሰብስቧል | 930 ብር ለአንድ ሰራተኛ ድጋፍ ተደርጓል:: |
| 6 | ብዙሃን መገናኛ | 893315 | ♦ በበኩር ጋዜጣ ትውልድ ይዳን በሚል ርዕስ መረጃዎች እየተዘጋጁ ለተለያዩ አካላት ተሠራጭቷል<br>♦ በሬዲዮ ጣቢያው የተለያዩ የፀረ ኤድስ ኘሮግራሞች ተላልፈዋል:: የማህበረሰብ ውይይት በቴሌቭዥን ጣቢያው ሽፋን ተሠጥቷል::<br>♦ በአማራ ቴሌቪዥን በየሳምንቱ አዝናኝና አስተማሪ የሆኑ ፕሮገራሞች ተላልፈዋል<br>♦ ለሚዲያ ባለሙያዎች ስልጠናዎች ተሰጥተዋል<br>♦ የተቐሙን አቅም በቁሳቁስ እንዲሙዋላ ተደርጎአል | - ከድርጅቱ በጀት ብር 25740 ለበኩር ጋዜጣ ብር 72930 በሬዱዩ ለሚዘጃ የፀረ ኤድስ ዘገባዎች ወጪ ተደርጓል:: |

| ተ.ቁ | መ/ቤት | ከሴክሬታሪት የተመደበ በጀት | ታቅደው የተፈፀመ ተግባራት | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| 7 | ሠማጉ | 100000.00 | ♦ ለ362 ወላጅ ላጡ ሕፃናት ድጋፍ ተደርጓል | |
| 8 | ሲቪል ሰርቪስ | | ♦ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች የፀረ ኤድስ ትምህርት ተሠጥቷል | |
| 9 | ሴቶች ጉዳይ | 90344.00 | ♦ ሴቶች ልጃገረዶችና ኤች አይ ቪ/ኤድስ በሚል ርዕስ 204 ሰዎች የተሳተፉበት አውደ ጥናት ተካሂዷል:: | |
| 10 | ጥቃቅናን አነስተኛ የንግድ ሥራዎች | - | ♦ የፀረ ኤድስ ትምህርት ያነገቡ ሦስት አይነት በራሪ ወረቀቶች ተዘጋጅተው ተሠራጭቷል::<br>♦ ለ140 የመ/ቤቱ ሠራተኞች ሥልጠና ተሠጥቷል<br>♦ በንግድ ምክር ቤቶች በኩል የፀረ ኤድስ ሥራ እንዲተገበር ጥረት ተደርጓል | |
| 11 | የሕብረት ሥራ ማህበራት ማስፈሪያ | - | ♦ ቢሮው ቮካን ለኢትዮትያ በማስተባበር 29549 ወንድና ለ2738 ሴቶች የፀረ ኤድስ ትምህርት የ5ቀን ስልጠና ተሠጠቷል:: ተሳታፊዎችም 9 ወረዳና ከ67 የህብረት ሥራ ማህበራት የተመለመሉ ናቸው:: | በቮካ ኢትዮጵያ ድጋፍ የተከናወነ |
| 12 | ትምህርት | 1400000.00 | ♦ የሥራ ላይ ፖሊሲ ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቷል<br>♦ በ23 የትምህርት ተቋመት የፀረ ኤድስ ትምህርት የሚሠጥባቸው ሚኒ ሚዲያ<br>♦ የማህበረሰብ ውይይት ወረዳዎች (ፎገራ መቂትና ሜጫ) ለመጀመር 66 ሰዎች ስልጠና ተሠጥቷል::<br>♦ 42 የፀረ ኤድስ ክበባት አባላት የአቻ ለአቻ ስልጠና ተሠጥቷል | |
| 13 | ፍትህ | - | ♦ ለ169311 ሰዎች በንቃተ ህግና አዲስ ዙሪያ ስልጠና ተሠጥቷል:: | ወጭ አይጠይቅም |
| 14 | ግብርናና ገጠር ልማት | 75000.00 | ♦ 45 የልማት ጣቢያ ሰራተኞች የባሕሪ ለውጥ ስርፀት ስልጠና ተሠጥቷል:: | |
| 15 | የክልሉ ሴቶች ማህበር | 18008.00 | ♦ ክልላዊ ጉባኤ ሲያ ዘጋጁ የገንዘብ ድጋፍ ከማድረግ ባሻገር ለግማሽ ቀን ከቀበለ ጀምሮ ለተገኙ 400 የሴቶች አመራር አባላት ስለ ሥነ ፆታና ኤች.አይ.ቬ/ኤድስ ጽሑፍ በማቅረብ ውይይት ተደርጓል:: ጠቃሚ ጉዳዮች ተነስተው በዚህ መዋቅር ከሰ ቶች ተጋላጭነት አንፃር አ ች.አይ.ቨ /ኤድስ ሜይንስትሪም መደረግ እንዳለበትና ከሰ ክሬታሪያቱ ጋር ተቀራርቦ በቅንጅት መሰራት እንዳለበት ስምምነት ላይ ተደርሷል :: | |

| ተ.ቁ | መ/ቤት | ከሴክሬታሪት የተመደበ በጀት | ታቅደው የተፈፀመ ተግባራት | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| 16 | የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት | - | ♦ በስራ ቦታ ላይ አ.ች.አይ.ቭ /ኤድስን ሜይንስትሪም ማድርግ በሚል ርዕስ ለሠራተኞቹ እንድናቀርብ በጠየቀው መሰረት ለግማሽ ቀን ለ20 ከፍተኛ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በተገኘ ነብት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ | በሴክሬታሪያቱ የተደረገ የነክኒክ ድጋፍ |
| 17 | ባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ | - | ♦ ለ60 የፖሊ. ቴክኒክና ዋናው ግቢ የአስተዳደር ሰራተኞች የግማሽ ቀን ወቅታዊ አ.ች.አይ.ቭ /ኤድስ ሁኔታና ሜይንስትሪም በማድርግ ምን እንደሚጠበቅባቸው ቅስቀሳ ተደርጓል | « |
| 18 | የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዩች ቢሮ | - | ♦ የፖሊስ ኮሚሽን የማሪያ ቤቶች አስተዳደርና የሚሊሽያ ጽ/ቤት የመለዮ ለባሽና ሲቪል ሠራተኞች በተገኙበት ለ100 ተሳታፊዎች ወቅታዊ የአ.ች.አይ.ቭ /ኤድስ ሁኔታን በማሳየት የመለዮ ለባሽን ተጋላጭነትና በሥራ ቦታ አ.ች.አይ.ቭ /ኤድስ ሜይንስትሪም ማድርግ እንዲሁም የኤድስ ፈንድ ስለማቋቋም የአንድ ቀን ጥልቅ ውይይት ተደርጓል፡፡ | « |
| 19 | ጣና በለስና የካጆ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት | 41290.00 | ♦ ፕሮጀክቱ በሚከናወንበት አካባቢ ያለውን የኤች.አይ.ቬ/ኤድስ ተጋላጭነት በመስክ በመገምገምና መነሻ በማዘጋጀት በዞኑ በኩል ለአካባቢው ህ/ሰብና ለፕሮጀክት ሰራተኛው የዞን የወረዳ የቀበሌና ሌሎችም አመራሮች በተገኙበት ለ200 ተሳታፊዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል፡፡ | በምዕ/ጎጃም አስተባባሪነት |
| 20 | የስራ አመራር ኢንስቲትዩት | - | ♦ ለ618 ሰልጣኞች የጤና እና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ | |
| 21 | የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር | | ♦ ለ120052 የህግ ታራሚዎችና አባላት የፀረ-ኤድስ ትምህርት ተሰጥቷል<br>♦ ለ100 የመ/ቤቱ አመራር አከላት የፀረ-ኤድስ ትምህርት ተሰጥቷል<br>♦ ለ100 ሰልጣኝ የማረ/ፖሊስ አባለት የፀረ-ኤድስ ትምህርት ተሰጥቷል | |

## የ1998 የበጀት ዓመት የሴክተሮች ሪፖርት ( ሠንጠረዥ 13 )

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባራት | መለኪያ | የዓመት ዕቅድ | ክንዉን | ስራ ላይ የዋለ በጀት | የበጀት ምንጭ | ተጠቃሚ በፆታ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ወ | ሴ |
| የገጠር መንገዶች ባለስልጣን | | | | | | | | |
| 1 | የ1998 የበጀት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅ ኀል | ጥራዝ | 1 | 1 | - | - | 2296 | 255 |
| 2 | የኤድስ ፈንድ ማቋቋ ያ የመመስረቻ ጽሑፍ መተዳደሪያ ደንብ ተዘጋጅቷል | ጥራዝ | 1 | 1 | 566 | ከባለስልጣኑ | 2296 | 255 |
| 3 | መተዳደሪያ ደንቡን በሠራተኛዉ በማፀደቅ ማህበሩን ማቋቋም | ፐርሰንት | 100 | 100 | 120 | ከባለስልጣኑ | 2296 | 255 |
| 4 | ማህበሩ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ህጋዊ እዉቅና እንዲያገኝ ተደር ኀል | ፐርሰንት | 100 | 100 | 100 | - | 2296 | 255 |
| 5 | ለፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተግባት በጀት ለመመደብ በባለስልጣኑ መ/ቤት ስምምነት ተደርሶአል፡፡ | | | | | | | |
| የማህበራዊ ዋስትና | | | | | | | | |
| 1 | የተለያዩ የመረጃ ቁሳቁሶችን በማሰባሰብ ለሠራተኛዉ እንዲደርስ ተደር ኀ ል | ቁጥር | 300 | 30 | - | HAPCO, OSSA | 36 | 23 |
| 2 | ወላጆቻቸዉን ላጡ ህፃናት እገዛ ለማድረግ ከሠራተኛዉ ገንዘብ መሰብሰብ | ብር | 600 | 507 | - | ከሠራተኛዉ | - | - |
| 3 | የተለያዩ አካላት ባዘጋጁዋቸዉ ስልጠናዎች መ/ቤቱ ተሳታፊ ሆኖአል | ቁጥር | 10 | 5 | - | ልየ ልዩ አካላት | 2 | 3 |
| የአካባቢ ጥበቃና የመሬት አስተዳደር | | | | | | | | |
| 1 | የፀረ-ኤች/አይ.ቪ/ኤድስ ረቂቅ ደንብ ማዘጋጀት | | 1 | ረቂቅ ደንቡ ተዘጋጅቶ በሃለፊዎች ታይቷል | | | | |
| 2 | በፊልምና በባለሙያ የተደገፈ ትምህርት ተሰጥቶአል | ቁጥር | 12 | 8 | 3500 | ከመ/ቤቱ | 320 | 80 |
| 3 | ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ትምህርት ተሰጥቶአል | ሠዉ | 1880 | 750 | ከሌሎች ስራዎች ጋር | ከመ/ቤቱ | 730 | 100 |
| 4 | በመ/ቤቱ መጽሔትና በራሪ ወረቀቶች ላይ መልዕክቶችን ማስተላለፍ | ጊዜ | 2 | 1 | 2000 | ከመ/ቤቱ | - | - |
| ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | | | | | | | | |
| 1 | በኮሚሽኑ በሚሰጡ ልዩ ልዩ ስልጠናዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ማካተት | ዞን | 4 | 4 | ከሌሎች ስራዎች ጋር | ፒስንፐ | 800 | - |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | በኮሚሽኑ መጽሔት ጠቃሚ ጸሑፎን ማስተላለፍ | | 2 | 2 | | ኮሚሽኑ | - | - |
| 3 | ወረርሽኙ እያደረሰ ያለዉን ጉዳት ለመዳሰስ ፕሮፖዛል ተዘጋጅቷል፡፡ | ጥራዝ | 1 | 1 | | | | |
| የሴቶች ጉዳይ ቢሮ | | | | | | | | |
| 1 | የሴቶችን ተጋላጭነት ለመቀነስ በመጽሔት ጽሮሞሽን ስራ ተሰርቷል | | ከዕቅድ ዉጭ | - | 500 | - | - | - |
| 2 | ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ እይስከተለ ስላለዉ ጉዳት ክልል አቀፍ የዉይይት መድረክ ማዘጋጀት | መድረክ | ከዕቅድ ዉጭ | 204 | 90344 | ሴክሬታሪይት | 29 | 175 |
| ምዕ/ዕዝ መከላከያ | | | | | | | | |
| 1 | የምዕራብ ዕዝ ዋና አዛዦች የኤድስ ኮንፈረንስ ማካሄድ | መድረክ | | 80 ፐርሰንት | 23038 | ሴክሬታሪይት | 70 | - |
| 2 | ከሻምበል እስከ ክ/ጦር ኮማንደር የአንድ ቀን የጋራ ዉይይት ማድረግ | መድረክ | | 90 ፐርሰንት | በጀት አይፈልግም | ሴክሬታሪይት | 398 | - |
| 3 | በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የደም ምርመራ መቀስቀስና ማካሄድ | ቁጥር | ፈላገዉ | 3182 | በጀት አይፈልግም | - | 3022 | 160 |
| 4 | የአቻ መሪዎች ስልጠና | ቁጥር | - | 1810 | 70000 | መከላከያ | 1810 | |
| የወጣቶችና ስፖርት | | | | | | | | |
| 1 | ለፀረ-ኤድስ ክበባትና በቁሳቁስ ማጠናከር | ቁጥር | 20 | 20 | 12456 | ሴክሬታሪይት | - | - |
| 2 | የወጣት ማዕከላትን ማጠናከር | ቁጥር | 15 | 15 | 597788 | ብሔራዊ ሴክሬታሪይት | | |
| 3 | በIT የቢሮዉን አቅም መገንባት | ቁጥር | 1 | 1 | 25000 | ሴክሬታሪይት | | |
| 4 | በባህር ዳር ከተማ ሞዴል ሁለገብ የወጣቶች ማዕከል መገንባት | ቁጥር | 1 | 1 | | ብሔራዊ ሴክሬታሪይት | | |
| ትምህርት ቢሮ | | | | | | | | |
| 1 | ለ23 የትምህርት ተቋማት የሚኒ ሜዲያ ዕቃዎች ማሙዋላት | ቁጥር | 23 | 23 | 685452 | UNDP | | |
| 2 | በተመረጡ ሶስት ወረዳዎች የማህበረሰብ ዉይይት ማካሄድ | ጣቢያ | 18 | 18 | 47190 | UNICEF | 660 | 417 |
| 3 | በተመረጡ ሶስት ወረዳዎች | ወረዳ | 3 | 3 | | WFP | 45 | 492 |

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባራት | መለኪያ | የዓመት ዕቅድ | ክንዉን | ስራ ላይ የዋለ በጀት | የበጀት ምንጭ | ተጠቃሚ በፆታ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ወ | ሴ |
| የፓርኮች ልማት | | | | | | | | |
| 1 | በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የዉይይት መድረክ በማዘጋጀት ለሠራተኛዉ ግንዛቤ መፍጠር | መድረክ | 2 | 2 | 164 | መ/ቤቱ | 25 | 4 |
| 2 | ለኢኮ ቱሪዝም ማህበራት አመራር ግንዛቤ መፍጠር | ቁጥር | - | 39 | 341 | መ/ቤቱ | 39 | - |
| 3 | ለአርሶ አደሮች ትምህርት መስጠት | ቁጥር | - | 1262 | 70 | መ/ቤቱ | 1193 | 69 |
| 4 | ከሠራተኛዉ የገንዘብ መዋጮ ማድረግ | ብር | 266 | 266 | - | ሠራተኛዉ | 52 | 7 |
| | **ብዘሃን መገናኛ** | | | | | | | |
| | በበኩር ጋዜጣ በየ15 ቀኑ አንድ ሙሉ ገፅ (ትዉልድ ይዳን) የኤች አይቪ ሽፋን መስጠት | በገፅ | 26 | 26 | 51’480.00 | መ/ቤቱ | የሬዲዮ አድማጮች | |
| 2 | በአማራ ሬድዮ በመደበኛ ፕሮገራም የኤች አይቪ መረጃዎችን ማስተላለፍ | በደቂቃ | 1560 | 1560 | 145’860.00 | መ/ቤቱ | የሬዲዮ አድማጮች | |
| 3 | የማህበረሰብ ዉይይት መደበኛ ፕሮገራም በሳምንት 2 ቀን ለ 30 ደቂቃ በሬድዮ ማሰራጨት | በደቂቃ | 780 | 780 | 44’880.00 | መ/ቤቱ | የሬዲዮ አድማጮች | |
| 4 | በኤፍ.ኤም ባህር ዳር በሳምንት 2 ቀን የአንድ ሰዓት የኤች.አይ.ቪ. ፕሮግራም ስረጭት በሬድዮ | በደቂቃ | 1560 | 1560 | 154’440.00 | መ/ቤቱ | የሬዲዮ አድማጮች | |
| 5 | በቴሌቪዥን የማህበረሰብ ዉይይትና ስልጠና በፕሮገራም ሽፋን መስጠት | በደቂቃ | 20 | 20 | 164’000.00 | መ/ቤቱ | | |
| 6 | በዩኒሴፍ ድጋፍ በክልሉ የወጣቶች ኤች አይ.ቪ. ኤድስን የመከላከል እንቅስቃሴዎችን ቀረፃ | በደቂቃ | 30 | 30 | 11’488.60.00 | መ/ቤቱ | | |
| 7 | ስለኤች አይ.ቪ. ኤድስ በቴሌቪዥን አጫጭር ድራማ ማስተላለፍ | በቁጥር | 12 | 12 | 600’090.40 | RHAPCO | | |
| 8 | ለጋዜጠኞች ስለኤች አይ.ቪ. ኤድስና የአዘጋገብ ስርዐት ስልጠና መስጠት | በቁጥር | 123 | 123 | 229’327.7 | RHAPCO | ወንድ=81 ሴት=42 | |
| 9 | ስለ ኤች አይ.ቪ. መረጃ ለማጠናከር የሚረዳ ኮምፒዩተረ፤ ቴፕ፤ፕሪንተር መግዛት | በቁጠር | 2 | 2 | 47’824.98 | RHAPCO | | |
| 10 | ለባንክ አገልግሎት ክፍያ መፈፀም | በብር | | | 100.53 | RHAPCO | | |
| | ድምር | | | | 1’449’392.25 | | | |

**በሴክትር መ/ቤቶች ደረጃ የተሰሩ ዋና ዋና ተግባራት ማጠቃለያ**

1. ትምህርት ቢሮ
   - ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ መምህራንና ሠራተኞችን የስራ ሁኔታ ለማመቻቸት ረቂቅ የኤድስ ፈንድ መመሪያ ተዘጋጅቷል
   - በትምህርት ቤት ፀረ ኤድስ ክበባት በሚኒሚዲያ በስነጽሑፍ በድራማ በጭዉዉት ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ በመከላከልና በድጋፍና እንክብካቤ ዙሪያ ትምህርትና ቅስቀሳ ተደርጓል፡፡
2. ወጣቶችና ስፖርት
   - በስነ ተዋልዶ፣በስርዓተ ፆታና በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ 514148 ወጣቶች ግንዛቤ አግኝተዋል
   - ለ467 ክበባትና ማህበራት የመፃሐፍት፣ቴሌቪዥንና የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁሶች ድጋፍ ተደርጓል፡፡
   - ወላጆቻቸዉን ላጡ ህፃናጽ ድጋፍ ለማድረግ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይና ከሴክሬታሪያት ጋር በመሆን ፕሮፖዛል በማዘጋጀት የ600000 ብር ድጋፍ ተገኝተል፡፡
   - 98 የወጣት ማዕከላትን እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡
   - በክልሉ የሚካሄደዉን የፀረ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ ለማገዝ በቢሮዉ በኩል የባለሙያ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
   - ቢሮዉ ኤድስ ፈንድ በማቋቋም ሶስት ወላጆቻቸዉን ያጡ ህፃናጽን በመያዝ በወር አንድ መቶ ብር ለእያንዳንዳቸዉ ድጋፍ በማድረግና የትምህርት ቤት ቁሳቁስ በማቅረብ እያስተማረ ይገኛል፡፡
   - ለሠራተኛዉ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት እንዲሰጥ አድርጓል፡፡
3. የህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ
   - ከቮካ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር በተለያዩ ወረዳዎች ለሚገኙ 29543 ወንድና 2738 ሴት የአመራር አካላትንና የመሠረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት አባላትን ለአምስት ቀናት ሁለገብ የሆነ ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡
   - በሌሎች መድረኮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተከናዉነዋል
   - የትምህርትና መረጃ ቁሳቁስ በማዘጋጀት እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡
4. ፍትህ ቢሮ
   - ለ154 ወንድና ለ145 ሴት ተሳታፊዎች ለአንድ ቀን በቪዲዮ የተደገፈ በማግለልና መድልዎ ዙሪያ ትምህርትና ዉይይት ተደርጓል፡፡
   - የሴቶችን የንብረት ባለቤትነትና የዉርስ መብት ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር በማያያዝ ለ161 ዐቃቢነህግ፣ለ172 ዳኞችና ለ88 መርማሪ ፖሊሶች ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡
   - ለፍትህ ፈላጊዉ ህ/ሰብ ስለጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ትምህርት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

የአጋጠሙ ችግሮች

- በሴክሬታሪያቱ በኩል የሚደረገዉ የገንዘብ ድጋፍ አናሳ መሆንና በወቅቱ አለመለቀቅ
- የፀረ ኤድስ ክበባትን አቅም ለማሳደግ የበጀት እጥረት
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚሰጡ ትምህርቶች ተደጋጋሚ መሆንና ህ/ሰቡ መሰልቸት
- የፀረ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ማህበር ለማቋቋም የሃላፊዎች ትኩረት አለማግኘት
- መደበኛ በጀት አለመመደብ
- በስራ ክፍሎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪም አለመደረ
- ለኤድስ ፈንድ አመራር በቂ ስልጠና አለመሰጠት

### 3.2.2 ፓርትነርሽፕ

በፈፃሚ በአካላት የሚከናወኑ የፀረ ኤድስ ሥራዎች ቅንጅት እንዲኖራቸው የጋራ የትብብር ፎርሞች ተመስርተዋል፡፡ በ1998 የበጀት ዓመት ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመዋጋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ተብሎ የተመሠረቱት የፖርትነርሽኘ የትብብር ፎረሞች፡

- መንግስት ሴክተር መ/ቤቶች
- ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና
- ክልላዊ ፎረሙ ናቸዉ፡፡ሌሎች ማለትም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣የሲቪክ ማህበራት፣ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ማህበራትና የሜዲያ ፎረሞችም በ1997 የበጀት ዓመት ተቋቁመዋል፡፡

በዚህም መሠረት የተጠናከረና በሚጠበቀዉ ደረጃ ባይሆንም አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፡፡

የትብብር ፎረሞቹ አስተባባሪ ግብረ-ሃይል ያቋቋሙ ሲሆን ፎረሞቹ እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ ተከታታይ ስብሰባዎችን በማካሄድ ቅድመ-ዝግጅቶች አድረገዋል፡፡ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሠዎች ማህበራት በተሻለ ሁኔታ እየተንቀሳቀሱ ሲሆን ጽ/ቤት በመክፈትና የሠዉ ሃይል የተቀጠረላቸዉ ሲሆን በክልሉ የሚገኙ ከ64 በላይ ማህበራትን በጋራ በማገናኘት የጠቅላላ ጉባዔ በማካሄድ ጠቃሚ ስራዎችን አከናዉነዋል፡፡ በመስክ በመንቀሳቀስም በየደረጃዉ ካለዉ አመራር ጋር ዉይይት በማድረግ ድጋፎች እንዲገኙ፣ግንኙነቶች እንዲዳብሩ አበረታች ስራዎችን አከናዉነዋል፡፡

በሜዲያ በኩልም የተጠናከረ ባይሆንም ለሜዲያ ባለሙያዎች ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጎአል፡፡ ሌሎችም በጅምር እንቅስቃሴ ላይ የገኛሉ፡፡

### 3.2.2 ሌሎች

የፈፃሚ አካላትን አቅም በስልጠና ከማገዝ ባሻገር በገንዘብና በቁሳቁስ ለማሳድግ ጥረት የተደረገ ሲሆን በ1998 የበጀት ዓመት ለመንግስት ሴክተሮች፣መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች፣ለሲቪክ ማህበራት፣ለግል ድርጅቶችና ለሐይማኖት ተቋማት የብር 54,256,504 ድጋፍ ተደርጎአል።

በጤናዉ ዘርፍም የጤና ተቋማትን በመገንባት፣በማስፋፋትና የዉስጥ ዕቃዎችንና አቅርቦት በማሙዋላት በኩል ከፍተኛ ስራዎች ተከናዉነዋል። በዚህም መሠረት የጤና ኬላዎች ግንባታ፣የጤና ድርጅቶች ማስፋፋት፣ኮምፒዩተሮችና ሌሎች ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጎአል።

በትምህርት ሴክተሩም 23 የፀረ-ኤድስ ክበባትን በሚኒሜዲያ በማጠናከር በትምህርት ቤቶች ዉስጥ ያለዉን ማህበረሰብ ለማስተማርና ለመቀስቀስ እንዲቻል ጥረት ተደርጎአል።

ከትምህርት ቤት ዉጭ ላለዉ ወጣትም የወጣት ማዕከላት እንዲገነቡና እንዲጠናከሩ፣የመረጃ ማዕከላት እንዲስፋፉና የዉስጥ ቁሳቁሶች እንዲሙዋሉ ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ጥረቶች ተደርገዋል። በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር በክልል ደረጃ አንድ የመረጃ ማዕከል(resource center) ተቋቁሞ አገልግሎት ለመስጠት በዝግጅት ላይ ይገኛል። በተለያዩ ዘርፎች በክልል፣በዞንና በወረዳዎች የቴክኒክ ድጋፎች ተደርገዋል።

## 4. መንግስታዊ ያልሆኑ ድረጅቶች እና ማኅበራት ተሳትፎ

በክልሉ የሚካሄደውን የኤች አይ ቪ/ኤድስ የመከላከልና መቆጣጠር ስራዎች በማስፈፀምና የበጀት ድጋፍ በማድረግ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እያደረጉ ያሉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። በ1998 ዓ.ም በተደረጉት የመከላከልና መቆጣጠር ተግባራት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማኅበራት ያከናወኗቸው ተግባራራት በዞን ደረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል።ምንም እንኳዋ በክልሉ የሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር እየተንቀሳቀሱ ቢሆንም የሚያከናዉኑዋቸዉን ተግባራት ወቅቱን ጠብቀዉ ሪፖርት በማድረግ በኩል ዉስንነት ይታያል። በመሆኑም በሁሉም ደረጃ የተጠናከረ የሪፖርት ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነዉ።

- መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎ የተከናወኑ ተግባራት( ሠንጠረዥ 14)

| ተቁ | ዞን | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | የተከናወኑ ተግባራት በጥቅል |
|---|---|---|---|
| 1 | ሰሜን ሸዋ | 1. ሰዎች ለሰዎች | የማህበረሰብ ውይይት |
| | | 2. ወርልድ ቪዥን | የማህበረሰብ ውይይት |
| | | 3. ክርስቲያን ህፃናት መረጃ | » |
| | | 4. ቀይ መስቀል | » |
| | | 5. የኢት.ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን | ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት እንክብካቤ |
| | | 6. አዲስ ኪዳን | » |
| | | 7. አክሽን ኤይድ | » |
| 2 | ደቡብ ጐንደር | 1. ኤፍ ኤች አይ | IEC/BCC |
| | | 2. አመልድ | » |
| | | 3. ወርልድቪዥን | » |
| | | 4. MSF-Greeec | » |
| | | 5. CPAR-ETh. | » |
| | | 6. Pathfinder | » |
| | | 7. EOC/DICAC | ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | 8. ፀረ ወባ ማህበር | » » |
| | | 9. ዋቢ የህፃናት መርጃ ማዕከል | » » |
| | | 10. CVM | » » |
| | | 11. አክሽን ኤይድ | » » |
| | | 12. አ ..ኦ.ሰ | ድጋፍና እንክብካቤ |
| 3 | ምስ/ጐጀም | 1. CVM | IEC/BCC, ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | 2. SIDA | IEC/BCC |
| 4 | ምዕ/ጐጀም | 1. CVM | • IEC/BCC<br>• ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | 2. People to People | • IEC/BCC<br>• ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | 3. World Vision | • IEC/BCC<br>• ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | 4. Red Cross | • አመቻቾችን አሰልጥኖ CCE እንዲጀመር አድርጓል |
| 5 | ባ/ዳር | 1. CVM | |
| | | 2. FHI/OSSA | IEC/BCC<br>ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | 3. ኢየሩሳሌም የህፃናት መርጃ | |
| | | 4. EOC/DICAC | |
| | | 5. ፀረ ወባ | |
| | | 6. FSC ( Focus on street children) | |
| | | 7. መቅድም ኢትዮጵያ | |
| | | 8. ተስፋ ጐህ | |
| | | 9. ህብረተሰብ አቀፍ የማህበረሰብ ልማት ካውንስል | |
| | | 10. CBOs (Iddirs) | |
| | | 11. ኬር ባህር ዳር | |

| ተቁ | ዞን | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | የተከናወኑ ተግባራት በጥቅል |
|---|---|---|---|
| **6** | ሰ/ጐንደር | **1.** CVM | IEC/BCC<br>ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | **2.** ማህበረ ህይወት | » |
| | | **3.** አክሽን ኤይድ | » |
| | | **4.** ዩኒሴፍ | » |
| | | **5.** ወርልድ ቨ ዥን | VCT አገልገሎት መስጫ ማዕከል አስከፍቷል |
| | | **6.** OSSA | ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | **7.** አመልድ | ሜይንስትሪሚንግ እና CCE ስራዎችን ያከናውናል |
| | | **8.** ANPPCAN | IEC/BCC<br>ድጋፍና እንክብካቤ |
| **7** | ዋግ ኽምራ | **1.** አክሽን ኤይድ<br>**2.** EOC<br>**3.** COPEE<br>**4.** SC | IEC/BCC<br>ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | **5.** ዮኒሴፍ | » |
| **8** | አዊ | **1.** CVM | IEC/BCC<br>ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | **2.** አክሽን ኤይድ | » |
| | | **3.** ዮኒሴፍ | » |
| **9** | ኦሮሚያ | **1.** ዮኒሴፍ | IEC/BCC<br>ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | **2.** ወርልድ ቪዥን | » » |
| | | **3.** ሙስሊም ኤጀንሲ | » » |
| | | **4.** Intra Health | PMTCT |
| **10** | ደቡብ ወሎ | **1.** ዮኒሴፍ | IEC/BCC<br>VCT/PMTCT<br>ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | **2.** SC | |
| | | **3.** OSSA | |
| | | **4.** አድማስ ጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት | |
| | | **5.** ቤተሰብ መምሪያ | |
| | | **3.** SIDA | IEC/BCC |
| **11** | ሰሜን ወሎ | **1.** PADET | IEC/BCC<br>ድጋፍና እንክብካቤ |
| | | **2.** SC-UK | |

በክልል ደረጃ በቀጥታ ሪፖርት ያደረጉ መያዶች (ሠንጠረዥ 15)

| ተ.ቁ | የድርጅቱ ስም | ዋና ዋና ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | ወርልድ ቪዝን | በሰ/ጎንደር በ3 ወረዳዎች ለህይወት ክህሎት ስልጠና፣ ለVCT ግንባታ፣ ለአባለዘር ህክምና ድጋፍ በሩብ ዓመቱ ብር 403,900 መድቦ ስራ ላይ አውሏል:: |
| 2 | ሙቭ | በጎንደርና በባህር ዳር ዩንቨርሲቲዎች ለ683 ተማሪዎች የባህሪይ ለውጥ ስርፀት ተግባራትን አከናውኗል:: |
| 3 | ኤፍ.ኤች.አይ | ለ79 ሰዎች የART Adherence ስልጠና ለ5 ቀናት ሰጥቷል |
| 4 | ኬር ባህርዳር | የካውንስሊንግ ክፍሎች በት/ቤቶች መገንባት፣ የባህሪ ለውጥ ስርፀት፣ VCT ማዕከላትን ማጠናከር፣ በድጋፍና እንክብካቤ፣ የአጋር ድርጅቶችን አቅም ማጠናከር ተግባራትን ለማከናወን 371,918.50 ብር ስራ ላይ አውሏል:: |
| 5 | ቤተሰብ መምሪያ ደሴ | በባህሪ ለውጥ ስርፀት ስራ ሲያከናውን ቆይቷል |
| 6 | ዲኬቲ | • 6828875 ኮንዶም አሰራጭቷል:: |

## 4.1. የበጀት ድጋፍ የተደረገላቸው መያዶች

በ1998 የበጀት አመት ውስጥ ለክልሉ ሴክሬታሪያት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል አቅርበው፣ በጽ/ቤቱ ተቀባይነት አግኝተው የገንዘብ ድጋፍ ያገኙ መያዶች፣ የፀደቀላቸውና የተላለፈላቸው የገንዘብ መጠን እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል::

ከሴክሬታሪያቱ የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው መያዶች (ሠንጠረዥ 16)

| ተቁ | የድርጅቱ ስም | የተከናወኑ ተግባራት በጥቅል | የተፈቀደለት | የተላለፈለት |
|---|---|---|---|---|
| **1** | በእምነት ለወገን (ቡሬ) | ድጋፍና እንክብካቤ | **20,000.00** | **20,000.00** |
| **2** | CVM (ጐንደር) | ጥናት ማካሄድ | **15,000.00** | **15,000.00** |
| **3** | ደሴ ዓይነስውራን ማህበር (ደሴ) | IEC/BCC | **40,000.00** | **40,000.00** |
| **4** | ቤተሰብ መምሪያ (ባህርዳር) | - | **111,477.22** | **111,477.22** |
| **5** | FHI (ባ/ዳር፣ደሴ፣ጐንደር፣ኮምቦልቻ) | ድጋፍና እንክብካቤ | **945,035.60** | **730,258.49** |
| **6** | ጋምቢ ኃላ/የተ.የግ.ክሊኒክ (ባ/ዳር) | VCT | **99285.00** | **22,000.00** |
| **7** | ኦርዳ (ORDA) | - | **2,187.96** | **2,187.96** |
| **8** | ፖዴት (ወልዲያ) | VCT | **93,938.62** | **93,938.62** |
| **9** | ተስፋ ጎህ ባ/ዳር | ድጋፍና እንክብካቤ | **30,000.00** | **29,991.10** |
| **10** | ትልም ኢንተግሬትድ (ደሴ) | VCT | **44,910.00** | **44,910.00** |
| **11** | የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር (ባ/ዳር) | ድጋፍና እንክብካቤ | **30,000.00** | **24,785.61** |
| **12** | የተቀናጀ የማህ/ልማት | ድጋፍና እንክብካቤ | **40,000.00** | **40,000.00** |
| **13** | 64 ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ማህበራት | ድጋፍና እንክብካቤ | **5234792.00** | **4735100** |
| **14** | ሴቶች ማህበር (የክልል) | ዐውድ ጥናት | **66300** | **66300** |
| **15** | አይነ ስውራን ማህበር ደሴ ቅርንጫፍ | ዐውድ ጥናት | **26166** | **26166** |
| **16** | የግለሰብ አጥኚ | ጥናት | **5000** | **5000** |
| | ድምር | | **6,804,092.4** | **6,007,115** |

በተጨማሪም የተለያዩ ድርጅቶች/ማኅበራት ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉቻቸውን አቅርበው ከ UNAIDS ገንዘብ እንዲያገኙ የድጋፍ ደብዳቤ በፃፍንላቸው መሰረት ሻቃና ቤተሰቦቹ 150,000 ብር እና ደብረ ብርሃን ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ማኅበር 170,000 ብር እንዲያገኙ ተደርጓል

## 5. ፕሮጀክት ምዘና

ወጥና ግልፅ የሆነ የፕሮጀክት ምዘና ስርአት ከክልል እስከ ወረዳ በመዘርጋት በፈፃሚ አካላት ለሚቀርቡ የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄወች ፈጣንና ፍትሀዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ምዘና መመሪያ ተሻሽሎ ስራ ላይ ውሏል።በተጨማሪም በክልል ደረጃ ለሚቀርቡት የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄዎች ቀልጣፋና ፍትሀዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቴክኒካል ፕሮጅክት ምዘና ኮሚቴ ተቋቁሞ ስራ ጀምሯል። ለኮሚቴው ምዘና የሚያገለግል ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል ።

### 5.1. ከምግብ ዋስትና ለአስተያየት የተላኩ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች

**በ1998 የመጀት አመት ከክልሉ የምግብ ዋስትናና አደጋ መከላከል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተልከው በጽ/ቤታችን ሙያዊ አስተያየት የተሰጠባቸው ኘሮጀክት ኘሮፖዛሎች**

**ከምግብ ዋስትና ተልከው አስተያየት የተሰጠባቸው ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ( ሠንጠረዥ 17)**

| ተቁ | የኘሮጀክት አቅራቢው ድርጅት ሥም | የኘሮጀክቱ ርዕስ | ኘሮጀክቱ የሚተገበርበት ዞን/ወረዳ | የኘሮጀክቱ ቆይታ | ለኘሮጀክቱ የተመደበ በጀት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ | ይልማና ዴንሳ አካባቢ ልማት ኘሮግራም | ምዕ/ጎጃም ይልማና ዴንሳ | 5 ዓመት | 2338200 |
| 2 | ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ | ሊቦ ከምከም አካባቢ ልማት ኘሮግራም | ደ/ጐንደር | 5 ዓመት | 1756688 |
| 3 | ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ | ኤፍራታ ግድም አካባቢ ልማት ኘሮግራም | ሰ/ሸዋ | 5 ዓመት | 3588000 |
| 4 | የእንግሊዝ ሕፃናት አድን ድርጅት | ወጣት ተኮር የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና ደቡብ ወሎ ዞን | ደ/ወሎ | 1 ዓመት | 1468902 |
| 5 | ሲቪኤም | የኤች አይ ቪ/ኤድስ የመከላከልና የመቆጣጠር ኘሮግራም | 6 ዞኖች | 3 ዓመት | 3829188 |
| 6 | ANAPCAN | ህፃናትና ኤች አይ ቪ/ኤድስ | ሰ/ወሎ | 3 ዓመት | 1,957,133.00 |
| 7 | CVM | በምስ/ጐጃም ዞን የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ኘሮግራም | ምስራቅ ጐጃም | 3 ዓመት | 4,865,444.00 |
| 8 | PADET | ህፃናትና ኤች አይ ቪ/ኤድስ ፌይዝ 2 | ሰ/ወሎ | 3 ዓመት | 1850176 |
| 9 | የእንግሊዝ ሕፃናት አድን ድርጅት | በሰሜን ወሎና ዋግ ህምራ ኤችአይቪኤድስን ከምግብ ዋስትና ፕሮግራም ጋር ሜይንስትርይም ማድረግ | ሰሜንወሎና ዋግ ህምራ | 1 አመት | 2325000 |
| 10 | አፍሪካ የህፃናት ጥቃት መከላከል ኔትወርክ ኢትዮጵያ | ህፃናትና ኤችአይቪ ኤድስ ፌይዝ 2 | ሰሜን ወሎ | 3 አመት | 1957133 |
| | | | | ድምር | 25935864 |

## 5.2. የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄ የቀረበባቸው ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች

የተለያዩ ፈፃሚ አካላት ለሴክሬታሪያቱ የፕሮጀክት ድጋፍ ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን የድርጅቶቹ ሁኔታ እና የተሰጣቸው ምላሽ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**በጽ/ቤቱበ1998 በጀት ዓመት ቀርበው ምዘና የተካሄደባቸው ፕሮጀክት/ፕሮፖዛሎች ( ሠንጠረዥ 18)**

| ተቁ | የፕሮጀክት አቅራቢው ድርጅት ሥም | የፕሮጀክቱ ርዕስ | የሚተገበርበት ዞን/ወረዳ | የፕሮጀክቱ ቆይታ | የተጠየቀ በጀት | የተፈቀደ በጀት | የተሰጠ አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አፍሪካ ጃዝ መንደር | ሚዲያና ኤች አይ ቪ/ኤድስ | ባሕር ዳር | ወራት | 342000 | | በአካባበዉ ባሉ ክበባት መፈፀም ስለሚቻልተቀባይነት አላገኘም |
| 2 | የኢትዮጵያ አሰሪዎች ፌዴሬሽን የባ/ዳር ቅርንጫፍ | ኪነጥበብና ኤች አይ ቪ/ኤድስ | « | « | | 105967 | ተቀባይነት አላገኘም |
| 3 | ግለሰብ /አጥኚ/ | የሴቶች ተማሪዎችን ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ተጋላጭነት በደሴ ከተማ ጥናት ማካሄድ | ደሴ | 1 ጊዜ | 8045 | 5000 | ከማስተካከያ ጋር ተቀባይነት አግኝቷል |
| 4 | የአማራ ክልል ጤና ምርምር ላቦራቶሪ ማዕከል | በፈለገ ሕይወት ሆስፒታል ከደም ዝውውር ጋር በተያያዘ ዋና ዋና በደም የሚተላለፉ በሽታዎችን ለማጥናት የቀረበ ኘሮፖዛል | ባሕር ዳር | 1 ጊዜ | 11901 | 11901 | ተቀባይነት አግኝቷል |
| 5 | የአብክመ ግብርናና ተፈጥሮ ሃበት ቢሮ | የገበሬውን ህብረተሰብ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ በልማት ሰራተኞች አማካኝነት መከላከል | ክልል አቀፍ | 5 ወራት | 1032271 | | ከማስተካከያ ጋር ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ |
| 6 | የባህር ዳር ከተማ ም/ቤት ጽ/ቤት | የአቅም ግንባታ | ባ/ዳር | 3 ወራት | 341937 | | ተስተካክሎ እንዲቀርብ ተመልሷል፡፡ |
| 7 | የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚክስ ተማሪዎች ማህበር | የፀረ ኤድስ ዘመቻ | ባ/ዳርና ሌሎች ከተሞች | 1 ሳምንት | 27000 | | ከአንድ ዲፓርትመንት በተናጠል የመጣ በመሆኑተቀባይነት አላገኘ ም |
| 8 | ምዕ/ጐጃም ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት | ወጣቱ፣ መልከም አስተዳደርና ኤች አይ ቪ/ኤድስ ኮንፈረንስ | ባሕር ዳር | 2 ቀን | 51060 | | በእናት መስሪያ ቤቱ ያልመጣ በመሆኑተቀባይነት አላገኘም |

| ተቁ | የኘሮጀክት አቅራቢው ድርጅት ሥም | የኘሮጀክቱ ርዕስ | የሚተገበርበት ዞን/ወረዳ | የኘሮጀክቱ ቆይታ | የተጠየቀ በጀት | የተፈቀደ በጀት | የተሰጠ አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **9** | አብክመ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | ባለፉት አመታት ውስጠ የክልሉን የመንግስት ሠራተኞች ከኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና የባህሪ ለወጥ እንዲያመጡ በየደረጃው የተሰሩ ሥራዎች ምን ያህል ውጤታማ እንደነበሩ ለመገምገም የተዘጋጀ ኘሮጀክት ኘሮፖዛል | ክልል አቀፍ | **3** ወር | **56120** | | ከማስተካከያ ጋር ተቀባይነት አግኝቶ በቀጣዩ በጀት አመት ሊደገፍ ታቅዷል |
| **10** | የኢፌዲሪ አየር ሃይል ጠ/መምሪያ የጉና አየር ምድብ | የሚኒሚዲያ ዕቃዎች ችግር ለማቃለል ግዢ | ባ/ዳር | **1** ጊዜ | ይቁሳቁስ ጥያቄ | | ይቁሳቁስ ጥያቄ በመሆኑተቀባይነት አላገኘም |
| **11** | ኢ/አ/ተ/ቤ/ክ ሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ በማህበረ ቅዱሳን የባ/ዳር ንዑስ ማዕከል | የሕይወት ክህሎት | ም/ጉጀም | | | | ለድጋፍ በጀት ስላልተገኘ ሌላ ጊዜ ሊታይ ይችላል:: |
| **12** | የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ምስራቅ ጉጃም ዞን ቅርንጫፍ | በደ/ማርቆስ ከተማ የተገነባውን የወጣቶች የመረጃና የመዝናኛ ማዕከል የወስጥ ድርጅት በማሟላት ሥራ ማስጀመር | ደ/ማርቆስ | **1** ዓመት | **267112** | **2377458** | ከማስተካከያ ጋር ተቀባይነት አግኝቷል:: |
| **13** | ቻይልድ ሴንተርድ ዴቨሎኘመንት | ኤች አይ ቪ/ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር | ደጀን ከተማ | **3** ዓመት | **662025** | | የድግግሞሽ ስራ በመሆኑተቀባይነት አላገኘም |
| **14** | የክልል ሴቶች ማኅበር | የግንዛቤ ማጎልበቻ ፕሮጀክት | ባ/ዳር | 3 ቀን | 66300 | 66300 | ለሴክሬታሪያተ የአድቮኬሰ ͺ ስራ አመቺ በመሆኑ ተደግፏል |
| **15** | ጋምቢ ኃ.የተ.የግ.ማህበር | ለ2500 ሰዎች ቭ ͺሰ ͺቲ መስጠት | ባ/ዳር | 6 ወር | 77285 | 77285 | ድጋፍ ተደርጎለታል |
| **16** | በሲቪኤም በኩል ለጥናት የቀረበ | Factors affecting reproductive health | ሰ/ጎንደር | 3 ወር | 15000 | 15000 | ድጋፍ አግኝቷል |
| **17** | ሲቪኤም | በምስራቅ ጎጃም ዞን የኤችአይቪኤድስ መከላከል ፕሮግራም | ምስ/ጎጃም | 1 አመት | 587558 | | በጀት ሰላልተገኘ አልተደገፈም |
| | | | | **ድምር** | 2505298 | 2658911 | |

## 6. ስትራነጂክ እቅድ

የክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ከ1998 - 2002 ዓ.ም የሚጠቀምበት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ዘርፈ ብዙ ስትራቴጂክ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ቀርቧል፡፡

አሁን የወጣው የቀጣዩቹ አምስት አመታት የሚያገለግለው የኤች አይ ቪ/ኤድስ ዘርፈ ብዙ ስትራቴጅክ ዕቅድ ትኩረት በመካሄድ ላይ ያለውን እንቅስቃሴ ለማፋጠንና ለማጠናከር ነው፡፡ በዕቅዱ ውስጥ የዘርፈ ብዙው እንቅስቃሴ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግቦችና መርሆች ተመልክተዋል፡፡ ወረርሽኙን ለመቋቋም የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለማሳካትም ስድስት ወሳኝ ጉዳዮች ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡

እነዚህም የማስፈፀም አቅም ግንባታ፣ ህብረተሰቡን ማንቀሳቀስና አቅም ማጎልበት፣ ከጤና ኘሮግራሞች ጋር ቅንጅት መፍጠር፣ አመራርና ኤች አይ ቪ/ኤድስን በእንቅስቃሴ ማካተት፣ ማስተባበርና ቅንጅት መፍጠርና ልዩ ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሉት ናቸው፡፡

የስትራቴጂክ ዕቅዱ ከላይ የተመለከቱትን ስድስት ዋና ዋና ጉዳዩች ላይ በማተኮር ዋና ዋና የትኩረት ዘርፎችን ለያቶ አውጥቷል፡፡ በእያንዳንዱ የትኩረት ዘርፍ ውስጥ ዋና ዋና ጉዳዩችን አውጥቶ ስለእያንዳንዱ ዓላማና የተመረጡ ማስፈፀሚያ ስልቶች ተነድፈዋል ፡፡ ዙሪያ መለስ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስትራቴጂክ ዕቅድ በሠንጠረዥ የቀረበ ሲሆን የትኩረት ዘርፎች በ17 ዓላማዎች፣ ዋና ዋና ተግባራት፣ አመልካቾች፣ ማረጋገጫና የሚመለከታቸው አካላት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

ይሄን የአምስት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገው ወጪ ብር 1.7 ቢሊዮን እንደሚሆን የተገመተ ሲሆን የክልሉ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት፣ ሴክሬታሪያቱም በማስተባበር፣ ሃብት በማፈላለግና አፈፃፀሙን በመከታተል፣ ፈፃሚ አካላት አጋር ድርጅቶችና ህብረተሰቡ ጉልህ ተሳትፎና ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 7. የበጀት ምንጭ አጠቃቀም

በ1998 ዓ.ም በጀት ዓመት ከተለየዩ ረጂ ድርጅቶች የተገኘውን ሃብት በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል ከፍተኛ ጥራት ተደርጓል። በዚህም መሠረት የተገኘው የበጀት መጠንና አጠቃቀም ከዚህ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል።

የበጀት ምንጭና አጠቃቀም በድርጅት ደረጃ ( ሠንጠረዥ 19)

| ተ.ቁ | የበጀት ምንጭ | በ1997 ስራ ላይ የዋለ | በ1998 የበጀት አመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | የተገኘ | ስራ ላይ የዋለ (በብር) | % |
| 1 | አለም ባነክ | 15595284.00 | 10950954.00 | 9979348.00 | 91.13 |
| 2 | ግሎባል ፈንድ | 17161065.00 | 49184282.00 | 49026398.00 | 99.68 |
| 3 | አክሽን ኤይድ | 1799078.00 | 1061713.00 | 650965.00 | 61.31 |
| 4 | የዩኒሴፍ | 2325584.00 | 3051433.00 | 2767814.00 | 90.71 |
| 5 | ሲዳ | 2000000.00 | 400000.00 | 370801.61 | 92.70 |
| 6 | ጂ.ቲዜድ | 432236.00 | 265735.00 | 165119.00 | 62.14 |
| 7 | ዩኤንዲፒ | 788072.00 | 4644048.00 | 4040127.00 | 87.00 |
| 8 | መንግስት | 1200000.00 | 696532.00 | 691881.00 | 99.33 |
| 9 | ቆጋ | 38149.00 | 82878.00 | 82800.00 | 99.91 |
| 10 | **ጠቅላላ ድምር** | **41339468.00** | **70337575.00** | **67775253.61** | 96.36 |

እንዲሁም በበጀት አመቱ በ1997 ዓ.ም በጀት የተጠቀምነውን ብር 31,852,638.76 በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ኦዲተሮች ያስመረመርን ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ዩኤንዲፒ ፕሮግራም ከጥር 1997ዓ.ም እስከ ታህሳስ 1998 ዓ.ም ድረስ ያለውን ሂሳብ ብር 2897914.61 ከዩኤንዲፒ በመጡ ኦዲተሮች እንዲመረመር ተደርጓል ።

ኦዲት የተደረጉ በጀቶች ( ሠንጠረዥ 20)

| ተ.ቁ | የበጀት ምንጭ | የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|
| 1 | ዓለም ባንክ (ኢምሳፕ) | **25,772,521.47** |
| 3 | አክሽን ኤይድ | **1,823,288.62** |
| 4 | ዩኒሴፍ | **2,404,258.21** |
| 6 | ጂ.ቲዜድ | **534,745.23** |
| 7 | ዩኤንዲፒ | **795,297.60** |
| 8 | መንግስት | **472,527.63** |
| 9 | ቆጋ | **50,000.00** |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **31,852,638.76** |

## 8. ክትትልና ግምገማ

በክልሉ ዉስጥ እየተካሄዱ ያሉትን የፀረ-ኤች.ኤ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራሞች በተሳካ መንገድ እንዲከናወኑ ለማድረግ በየደረጃዉ በተለያዩ አካላት የክትትልና ግምገማ ስራዎች ተከናዉነዋል፡፡ በመሆኑም በክልሉና በየደረጃዉ ባሉ የሴክሬታሪያቱ ጽ/ቤቶችም በበጀት አመቱ ሰፊ የክትትልና ግምገማ ስራዎችን በማከናዎን የተገኙ ጠንካራ ስራዎችና  በስራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ተለይተዋል፡፡

ክትትልና ግምገማ የተደረገባቸዉ የስራ መስኮችም ወላጆቻቸዉን ላጡ ህፃናትና ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ሠዎች በሚደረጉ የድጋፍ፣እንክብካቤና የገቢ ማስገኛ ተግባራት፣ በልዩ ልዩ የፕሮጀክት አፈፃፀም፣ በማህበረሰብ ዉይይቶች፣በሚይንስትሪሚንግ፣በሂሳብ አያያዝ፣የክበባትንና የማህበራትን እንቅስቃሴዎች፣በልዩልዩ የጤና ፕሮገራሞች፣...ወዘተ ናቸዉ፡፡ እነዚህን ተግባራት ለማከናዎን የመስክ እንቅስቃሴ በማድረግ፣ በሩብ ዓመት የመደበኛ የስራ አፈፃፀም ግምገማዎች፣የሚላኩ ሪፖርቶችን በመጠቀም፣አልፎ አልፎም በየደረጃዉ በተካሄዱ መደበኛ የኤድስ ምክር ቤቶችና የስራ አመራር ስብሰባዎችን በማካሄድና በክልል ደረጃ የተቋቋሙትን የግንኙነት መድረኮች በመጠቀም ነዉ፡፡በተጨማሪም ከረድዔት ድረጅቶች ጋር ማለትም ከዩኒሴፍ፣ከዩኤን.ዲ.ፒ.፣ከብሔራዊ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤትና ሌሎች በዚህ ተግባር ላይ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

በመሆኑም መልካም ስራዎች ተጠናክረዉ እንዲቀጥሉና በስራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችም ወቅታዊ እልባት እዲያገኙ በየደረጃዉ ባሉ የሴክሬታሪያቱጽ/ቤቶች በኩልም ሆነ በሌሎች አካላት ጥረት ተደርጉዋል፡፡

ይሁን እንጅ በየደረጃዉ የሚካሄደዉ የክትትልና ግምገማ ስራ የሁሉንም አካላት ጥረት ሊያግዝ በሚችል ደረጃ ላይ እየተካሄደ ነዉ ለማለት አያስደፍርም፡፡ በተለይም ለስራዉ ከፍተኛ ሃላፊነት የተሰጣቸዉ በየደረጃዉ ያሉ የኤድስ ም/ቤቶችና የስራ አመራር ኮሚቴዎች በተፈለገዉ መጠን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ተግባራትን እየተከታተሉ አይደለም፡፡ ሌላዉ ደግሞ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሁሉም አጀንዳ እንደመሆኑ መጠን ሴክተሮችም ሆነ ሌሎች ፈፃሚ አካላት በመደበኛ የሩብ ዓመት የስራ ግምገማ በሚደርግበት ጊዜ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን እንቅስቃሴ እንደ አንድ የመገምገሚያ ነጥብ አለመያዙ ነዉ፡፡

በዚህ መሠረት የክትትልና ግምገማ ሥራዉ ከፍተኛ ትኩረት የሚያስፈልገዉ በመሆኑ የክልሉ ሴክሬታሪያት በየደረጃዉ ያለዉን የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ለማጠናከር በሠዉ ሃይል በአደረጃጀትና በዘመናዊ ቴክኖሎጅ ታግዞ የተሻለ የመረጃ ልዉዉጥ ለማድረግ ሰፊ ጥረት እየተደረገ ሲሆን ከተለያ ፈፃሚ አካላት ጋር ተቀናጅቶና ተናቦ ለመስራት አሁን የተጀመሩትን የፓርትነርሽፕ ፎረሞች በየደረጃዉ አጠናክሮ ለመሄድ ትኩረት ተሠጥቶታል፡፡

በተጨማሪም ለክትትልና ግምገማ ስራዎች የሚያግዙ መመሪያዎችንና ተጨማሪ ቅፆችን በማዘጋጀትና በዘርፉም የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን አጠናክሮ ለመስጠት የሚያስችል ስራ በቀጣይ ይከሄዳል ፡፡

በ1999 የበጀት አመት በየደረጃዉ ከፍተኛ ትኩረት ሊደረግባቸዉ የሚገቡ ተግባራት መከከል፡

- መደበኛ ጉባኤ ማካሄድ
- የስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ
- የመስክ ጉብኝት
- የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ
- የዕቅድ አፈፃፀምሪፖርት ዝግጅት ወዘተ በግንባር ቀደምትነት የገኙበታል፡፡

ከዚህ በሻገር የ1997 እና የ 1998 የበጄት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ለመገማገም ሐምሌ 3/1998 በክልል ደረጃ በተከሄደዉመደበኛ ጉባኤ የተሰጡ የአሰራር አቅጣጫዎችን መሉ በሙሉ በዕቅድ አከትቶ መተግበር እንዲቻል ከወደሁ ቅደመ ዝግጅት በዬደረጃዉ መደረግ የኖርበታል፡፡

## 9. አስተዳደር ነክ ተግባራት

በ1998ዓ.ም በሰው ሃይል አስተዳደርና ሌሎች የሥራ ዘርፎች በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል።

በየደረጃው የሚገኙ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤቶችን በሰው ሃይል ለማጠናከር የሰው ሃይል ቅጥር በየደረጃው ተፈጽሟል። ከአዲስ ሠራተኞች ቅጥር በፊትም ከክልል እስከ ወረዳ ድርስ ባሉ ክፍት የሥራ መደቦች ሠራተኞችን በዝውውርና በደረጃ ዕድገት በማወዳደር ክፍት የሥራ ቦታዎች እንዲሞሉ ጥረት ተደርጓል።

ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ በሚገኙ የሴክሬታሪያቱ ሠራተኞች መካከል ለተወሰኑ ሠራተኞች የደረጃ ዕድገት የተሠጠ ሲሆን ሁሉም በየደረጃው የሚገኙ ሠራተኞች የፕ ሮቪደንት ፈንድ ክፍያ እንዲከበርላቸው ተደርጓል።

የክልሉ ሴክሬታሪያት የማስተባበር አቅሙን የበለጠ በሰው ሃይል ለማደራጀት ከተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት ባለሙያዎች እንዲመደቡ ተደርጓል። በዚህ መሠረት በበጀት አመት መጀመሪያ ጀምሮ ሁለት አዲስ ባለሙያምች በድርጅቱ የበጀት ድጋፍ ለሴክሬታሪያቱ ተቀጥረዋል።

በአጠቃላይ በአሁኑ ሰዓት በክልሉ ሴክሬታሪያት ሥር 246 ሠራተኞች በሥራ ገበታ ላይ የሚገኙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 39 ሴት ሠራተኞች ናቸው።

**የሠው ሃይል ብዛት በክልልና በዞን ደረጃ ( ሠንጠረዥ 21)**

| ተ.ቁ | መ/ቤት | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዋናው መ/ቤት | 21 | 10 | 31 |
| 2 | ምዕ/ጐጃም | 19 | 2 | 21 |
| 3 | ምስ/ጐጀም | 26 | 4 | 30 |
| 4 | ደ/ጐንደር | 20 | 10 | 30 |
| 5 | ሰ/ጐንደር | 23 | 1 | 24 |
| 6 | ደ/ወሎ | 27 | 3 | 30 |
| 7 | ሰ/ወሎ | 12 | 2 | 14 |
| 8 | ሰ/ሸዋ | 37 | 4 | 41 |
| 9 | ዋግኽምራ | 6 | 0 | 6 |
| 10 | አዊ | 8 | 3 | 11 |
| 11 | ኦሮሚያ | 7 | 0 | 7 |
| 12 | ባ/ዳር ልዩ ዞን | 1 | 0 | 1 |
| | ድምር | 207 | 39 | 246 |

የሴክሬታሪያቱን አደረጃጀት በአዲስ መልክ እንደገና ለማዋቀር በተወሰነው መሰረት የመዋቅር፣ የደመወዝ እስኬልና የሥራ መዘርዝር ፕሮፖዛል ቀርቦ በማኔጅመንቱ ፀድቋል እንዲሁም የሴክሬታሪያት ሠራተኞች አስተዳደር መመሪያ ረቂቁ ቀርቦ በሠራተኛው ሙሉ ተሳትፎ አስፈላጊው ማሻሻያ ታክሎበት የተጠናቀቀና በማኔጅመንቱም እንደገና ታይቶ ከመዋቅሩ ጋር ለቦርድ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በአስተዳደር ዘርፍ ከአለፉት አመታት በተሻለ ሁኔታ የግዥ ሥራዎች፣የንብረት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም የሪከርድና መዝገብ ቤት አገልግሎት ጥራት ባለው ሁኔታ እንዲፈፀሙ ተደርጓል፡፡ እነዚህና ሌሎች ተግባራትም በቀጣይነት ሊተገበሩ ይገባል፡፡ በሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራም አፈፃፀም በኩልም ህ/ሰብ ፍላጎት መሠረት ያደረገ አገልግሎት እንዲኖር የመረጃ ደስክ ተቋቁሙዋል፣የዉጤት ተኮር ዕቅድ የአዘገጃጀትና የአፈፃፀም ግምገማ በስራ ላይ እንዲዉል ጥረት የተደረገ ቢሆንም በዚህ ላይ በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩ ችግሩን ለመቅረፍ ለ3 የስራ ሃላፊዎች በዉጤት ተኮር ዕቅድ ዝግጅት ስልጠና እንዲሰት ተደርጎአል፡፡

**10. <u>ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች</u>**

- መደበኛ ጉባኤዎች በየደረጃው አለመካሄድ
- በየደረጃዉ ያለዉ አመራር ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥራ ቁርጠኝነቱ ማነስ
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራሞች በመንግስትና በአካባቢ ሕ/ሰብ በጀት አለመታገዝ
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በየደረጃዉ በተለይም በመንግስት ሴክተሩ በኩል ሜይንስትሪም አለመደረግ
- ቅንጅታዊ አሠራር አነስተኛ መሆን
- ከአለም ባንክ የታቀደው በጀት አለመለቀቅና በዕቅድ የተያዘ ሥራዎች አለመፈፀም
- የድጋፍና እንክብንቤ አገልግሎት ፈላጊዎች ቁጥር በመጨመሩ ከበጀት አቅርቦት ጋር አለመጣጣም
- ለዞንና ለወረዳ ሴክሬታሪያት በደረጃው የሚደረገው ድጋፍ አነስተኛ መሆን
- የትራንስፖርት ወይም መኪና እጥረት
- ለተለያዩ ፈፃሚ አካላት የተለቀቀ በጀት በወቅቱ አለመወራረድ
- የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በየደረጃዉ አለመኖር
- ከተለያዮ አካላት ወቅታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት አለመቅረብ በተለይ አንዳንድ ዞኖች ሪፖርት ሲያደርጉ የሪፖርት ማቅረቢያ ቅፆችን ያለመጠቀም፣ ሪፖርቶቻቸው ግልፅ ያለመሆን ወይንም እርስ በእርሱ የሚጣረዝ መሆን፣

በዞናቸው ያሉትን መያዶች እንቅስቃሴ ሪፖርት ያለማድረግ፣ ሪፖርት ያደረጉትም እቅድ ክንውን በግልፅ የሚያሳይ ያለመሆን

- ሴክሬታሪያቱ ከተቋቋመ ቀላል የማይባል ጊዜ ያሳለፈ ቢሆንም በዚህ ጊዜ ውስጥ የራሱ የሆነ አደረጃጀት የደመወዝ እስኬልና ሰራተኛው መብቱንና ግዴታውን የሚያውቅበት የአስተዳደር መመሪያ ያለመኖሩ::በዚህም ምክኒያት ከፍተኛ የሆነ የሠራተኛ ፍልሰት መከሠት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ።

## 11. ዓርአያነት ያላቸዉና ተጠናክረዉ ሊተገበሩ የሚገባቸዉ ተግባራት

በ1998 በጀት ዓመት በዕቅድ ተይዘው በተለያዩ አካላት የተከናወኑ በርካታ ዓበይት ተግባራት አሉ:: ከነዚህ ተግባራት መካከል በመልካም የስራ እንቅስቃሴነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ተግባራት አሉ :: ከነዚህም መከከል ዋና ዋናዎቹ

- በክልሉ እየተካሄደ ያለዉ የማህበረሰብ ዉይይት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር እንዲሁም በልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ተጨባጭ ለዉጥ ያሳዩ መሆኑና ይህንንም ፕሮግራም ለማስፋፋት የሚያስችል አቅም መፈጠሩ፤
- የድጋፍና እንክብካቤ ተግባራት በህ/ሰቡ በባለቤትነት እየተያዙ መሆኑ
- በሜይንስትሪሚንግ ዘርፍ ጥቂት ሴክተሮች የኤች አይ ቪ/ኤድስን ጉዳይ በመደበኛ ስራቸው ውስጥ ማካተታቸዉ
- ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎቸ አምራች እንዲሆኑ እየተደረገ ያለዉ ድገፍ አጠክሮ ማስቀጠል
- በሁሉም ደረጃ ባይሆንም የአመራር አካላት ስራዉን በባለቤትነት በመያዝ በጀት መመደብና ክትትል ማድረግ
- በጥቂት የሴክተር መ/ቤቶችም የኤድስ ፈንድ መቋቋም መጀመሩ
- በክልሉ ያሉ ፈፃሚ አካላት በቅንጅት ለመስራት የሚያስችላቸው ፎረም መመስረቱ
- ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ማህበራት ቁጥር ከጊዜ ከ10 ወደ 75 ማደጉና አቅማቸዉ መገንባቱ፣ ለነዚህ ማህበራት የሰው ኃይልና የበጀት ድጋፍ መደረጉ፣
- ከተለያዩ ረጂ ድርጅቶት ጋር በቅንጅት መስራት መቻሉና የድጋፍና እንክብካቤ ስራው በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ላይ ማተኮሩ ስለሆነም የተረጅነት ስሜት መቀነሱ ናቸው::

## 12.በክልሉ የታዩ የለዉጥ አመላከቾች

በተለያዩ አከላት በተደረጉ ጥረቶች በርከታ የለዉጥ አመላከቾችና የግብ ስኬቶች ተመዝግበዋል፡፡ ለአብነተም ያህል፡-

- .በፈቃደኝነት ላይ ተመሰረተ የምክረና የደም ምርመራ ፈላጊዎች፤የፀረ-ኤች.አይ.ቪ መዳህኒት ተጠቃሚ ሰዉ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱ
- የማግለልና መድሎዎ ድርጊቶችና አመለከከቶች እየቀነሱ መሆኑ
- ሕብርተሰቡ በፀረ-ኤድስ ሥራዎች ላይ የጎላ ተሳተፎ መደረጉ፤ የድጋፍና እንክከቤ ሥራ ማ መጀመሩ
- ጎጅ ልማዳዊ ድረጊቶች እየቀነሱ መሆኑ
- የኮንዶም አጠቃቀምና ስርጭት ከአመት ወደ አመት እየጨመረ መሄዱ ወዘተ የሚሉት በግንባር ቀደምት መጥቀስ ይቻላል፡፡

# 13. አባሪዎች

## 1998 የበጀት አመት በሲዳ አማራ ገጠር ልማት ፕሮግራም የበጀት ድጋፍ የተከናወኑ የፀረ-ኤድስ ሥራዎች (አባሪ 1)

የአብክበ ኤች አይቪ ኤድስ መከ/መቆ/ ፅ/ቤት በ1998 በጀት አመት ጀምሮ ከሲዳ አማራ ገጠር ልማት ፕሮግራም ማስተባበሪያ ዩኒት ጋር በመተባበር የተጠናከረና ቀጣይነት ያለዉ የፀረ-ኤድስ ሥራዎችን ለማከሄድ የሚያስችል ፕሮግራም ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።
በዚህ መሰረት በ1998 በጀት አመት ብር 400000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ከድርጅቱ ለመ/ቤታችን ተመድቦ የተለያዩ ሥራዎችን ለማከሄድ ተችለል። ዝርዝር አፈፃፀሙ ከዚቀጥሎ ቀርቧል።

2 . የአቅም ግንባታ ሥራዎች

ከሲዳ አማራ ገጠር ልማት ፕሮግራም ማስተባበሪያ ዩኒት በተገኘዉ በጀት በበጀት አመቱ ከተከናዎኑት ዋና ዋና ሥራዎች መከከል:-

- ☞ ለ386 የጤና ኤክስተንሽን ሰራተኞች የማህበረሰብ ዉይይት የአመቻችነት ስልጠና ለ7 ቀናት ተሰጥቷል.
- ☞ 300 የክልል፤የዞንና የወረዳ የሴክሬታሪያት ሰራተኞች የተሳተፉበት የ1998 በጀት አመት እቅድ አፈፃፀም ግምገማ በባህር ዳርና ደሴ ከተማ ላይ ከሰኔ 1-7/1998 የተከሄደ ሲሆን በዚህ ወቅት በፋይናንስ አስተዳደር በመረጃ አያያዝ እንዲሁም በክትትልና ግምገማ ስራ የ1 ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል፡
- ☞ ለ12 የክልልና የዞን ከፍተኛ ባለሞያዎች የ13 ቀን የፕሮጄክት ቀረፃ የክትትልና ግምገማ ሥልጠና ተሰጥቷል፡
- ☞ 1 ባለሞያ ለልምድ ልዉዉጥ እስራኤል አገር ደርሶ ተመልሰል.።

በ1998 በጀት አመት በእቅድ ተይዘዉ በድርጅቱ የበጀት ድጋፍ የተከናወኑ ተግባራት ዝርዝር አፈፃፀም ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል።

### 2.1 የማህበረሰብ ዉይይት ዕቅድ አፈፃፀም

በምስ/ጎጃም ዞን በሚገኙ 10 ወረዳች የማህበረሰብ ዉይይት በማስጀመር የተጠናከረ የፀረ-ኤድስ ሥራ ለመሰራት ታስቦ በታቀደዉ እቅድ መሰረት በበጀት አመቱ አመረቂ ዉጤት እንዲመዘገብ ተደርጓል።
ከ193 ቀበሌዎች ለተመለመሉ 386 ሴት የማህበረሰብ ዉይይት አመቻቾች የ7ቀን ስልጠና ተሰጥቷል።በ1998 ከ3ተኛዉ ሩብ አመት ጀምሮ በ10 ወረዳዎች በድምሩ 100 ቀበሌች ላይ 6297 ሰዎች የሚሳተፉበት የማህበረሰብ ዉይይት በተጠናከረ መልኩ በመከሄድ ላይ ይገኛል።ከነዚህ የማህበረሰብ ዉይይት ተሳታፊዎች መከከል 2839 (45%) ሴቶች ናቸዉ።በአጠቃለይ የማህበረሰቡን ዉይይት ለማስጀመር እንዲቻል የክልሉ ኤች አይቪ ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤት ከሲዳ አማራ ገጠር ልማት ፕሮግራም ማስተባበሪያ ዩኒት ከተመደበለት በጀት ብር 9950 ለአንድ ወረዳ ለ3 ወር በመመደብ ሥራዉን አስጀምሯል።የተጀመረዉን የማህበረሰብ ዉይይት እዳይቋረጥ ወረዎዳች ከድርጅቱ ከተመደበላቸዉ በጀት እንዲመድቡ በመደረጉ ዉይይቱ ተጠናክሮ በመከሄድ ላይ ይገኛል።

የማህበረሰብ ዉይይቱ ከፍተኛ ተኩረት ያደረገባቸዉ የኤች አይቪ ኤድስን ሥርጭት በሚያባብሱ ባህላዊ እመነቶች ዙሪያ ነዉ።

- ያለድሜ ጋብች
- የሴት ልጅ ግርዛት
- ግግ ማስፈልፈል
- ዉሽማ ማበጀት
- ንቅሳትን እንደ ዉበት መበቁጠር መፈፀም
- ለድህነት የሚዳርጉ ተግባራትን መፈፀም ለአብንትም ያህል ከአቅም በላይ መደገስ፣ለቁጠባ ትኩረት አለመስጠት ወዘተ በሚሉት ጉዳዮች ዙርያ ትኩረት የማህበረሰብ ዉይይቱ በመከሄድ ላይ ይገኛል። ከፍተኛና የበሰሉ ዉይይቶች በማህበረሰቡ ከተከሄዱ በኋላ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ዉሳኔዎች ይደነገጋሉ።

እነዚህተግባራት በአግባቡ እንዲፈፀሙ በየደረጃዉ የሚገኙ የተለያዩ አከለት የተጠናከረናቀጣይነት ያለዉ ክትትልና የግምገማ ሂደቶችን በመፈፀም ከፍተኛ የቴክኒክ ድጋፍ ማደረግ ይጠበቅባቸዋል፡

**2.2 የበጀት አጠቃቀም**

**በ1998 በጀት አመት ከሲዳ አማራ ገጠር ልማት ፕሮግራም ማስተባበሪያ ዩኒት ብር 400000.00 የተመደበ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ብር 370801.61 ወይም 92 በመቶ ለተከናወኑ ተግባራት ክፍያ ተፈፅሟል።**

**1998 ዓ.ም የማህበረሰብ ዉይይት የተጀመረባቸዉ ወረዳዎችና የሰልጣኝ የአመቻቾች ብዛት. ሠንጠረዥ 1**

| ተ.ቁ | ወረዳ | መለኪያ | የማህበረሰብ ዉይይት ሰልጣኞች | | | ሰልጣኞች ብዛት በቀበሌ ደረጃ | የማ/ሰብ ዉይይት የተጀመረባቸዉ ቀበሌዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንዉን | % | | |
| 1 | አዋበል | በቁጥር | 56 | 56 | 100 | 26 | 10 |
| 2 | ማቻከል | በቁጥር | 34 | 34 | 100 | 17 | 10 |
| 3 | ባሶሊበን | በቁጥር | 32 | 32 | 100 | 16 | 10 |
| 4 | ጎዛምን | በቁጥር | 64 | 64 | 100 | 32 | 10 |
| 5 | ደባይ ጥላት ግን | በቁጥር | 30 | 30 | 100 | 15 | 10 |
| 6 | እነማይ | በቁጥር | 20 | 20 | 100 | 10 | 10 |
| 7 | እናርጅ እናዉጋ | በቁጥር | 20 | 20 | 100 | 10 | 10 |
| 8 | ደጀን | በቁጥር | 38 | 38 | 100 | 19 | 10 |
| 9 | ሸበል በረንታ | በቁጥር | 12 | 12 | 100 | 6 | 10 |
| 10 | ጎንቻ ሲሶ እነሴ | በቁጥር | 26 | 26 | 100 | 13 | 10 |
| 11 | ሀለት እጁ እነሴ | በቁጥር | 34 | 34 | 100 | 17 | 10 |
| 12 | ደብረ-ኤልያስ | በቁጥር | 20 | 20 | 100 | 10 | 10 |
| | ድምር | | 386 | 386 | 193 | 193 | 100 |

**የማህበረሰብ ዉይይት ተሳታፊዎችና የአመቻቾች ብዛት በወረዳ ደረጃ**

**ሠንጠረዥ 2**

| ተ.ቁ | ወረዳ | መስኪያ | የማህበረሰብ ዉይይት ተሳታፊዎች | | | የአመ ቻቾች ብዛት | የማ/ሰብ ዉይይት የተጀመረባቸዉ ቀበሌዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወ | ሴ | ድ | | |
| 1 | አዋበል | በቁጥር | 400 | 286 | 686 | 35 | 10 |
| 2 | ባሶሊበን | በቁጥር | 374 | 171 | 545 | 20 | 10 |
| 3 | ደባይ ጥላት ግን | በቁጥር | 262 | 270 | 532 | 43 | 10 |
| 4 | እነማይ | በቁጥር | 361 | 307 | 668 | 20 | 10 |
| 5 | እናርጅ እናዉጋ | በቁጥር | 382 | 368 | 750 | 34 | 10 |
| 6 | ደጀን | በቁጥር | 309 | 308 | 617 | 37 | 10 |
| 7 | ሸበል በረንታ | በቁጥር | 274 | 282 | 556 | 30 | 10 |
| 8 | ጎንቻ ሲሶ እነሴ | በቁጥር | 419 | 281 | 700 | 20 | 10 |
| 9 | ሀለት እጁ እነሴ | በቁጥር | 414 | 273 | 687 | 20 | 10 |
| 10 | ደብረ-ኤልያስ | በቁጥር | 263 | 293 | 556 | 40 | 10 |
| | ድምር | | 3458 | 2839 | 6297 | 299 | 100 |

የ1998 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በፊዚክል ሥራና በፋይናንስ አፈፃፀም ደረጃ ( ሠንጠረዥ 3)

| ተ.ቁ | የሥራ ዝርዝር | መለኪያ | የፊዚክል ሥራ | | | የፋይናንስ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንዉን | % | ዕቅድ | ክንዉን | % |
| 1 | የማህበረሰብ ዉይይት አመቻቾችን ማሰልጠን | በቁጥር | 386 | 386 | 100 | 100,000.00 | 91,595.14 | 92 |
| 2 | የማህበረሰብ ዉይይት ተሳታፊዎች መስተንግዶ | በቁጥር | 7000 | 6297 | 90 | 100,000.00 | 99,490.48 | 99 |
| 3 | የ1998 የ9 ወር ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ መከሄድ | ተሳታፊ | 300 | 300 | 100 | 180, 000.00 | 159,774.09 | 93 |
| 4 | ከአገር ዉጭ ለልምድ ልዉዉጥ ባለሞያ መላክ | ሰዉ | 1 | 1 | 100 | 6,802.00 | 6,802.00 | 100 |
| 5 | የፕሮጀክት፤የክትትልና ግምገማ ስልጠና መስጠት | ሰዉ | 14 | 12 | 86 | 13198.00 | 13,139.30 | 99.5 |
| | ድምር | | | | | 400000.00 | 370,801.61 | 92 |

**1998 ዓ.ም በአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ የገንዘብ ድጋፍ የተከናወኑ ተግባራት (አባሪ 2)**

| | የሥራ ዝርዝር | መለኪያ | የፊዚካል ሥራ | | | የፋይናንስ ስራ | | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | % | የተገኘ | ክንውን | % | |
| 1 | ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ማህበራት ድጋፍ | ቁጥር | 42 | 41 | 97.6 | 200000 | 181000 | 90.5 | |
| 2 | ሴቶች ልጃገረዶችና ኤች አይ ቪ/ኤድስ አውደጥናት | » | 9 | 9 | 100 | 100000 | 90343.5 | 90.3 | |
| 3 | ድጋፍና እንክብካቤ አገለግሎት በ3 ወረዳች | » | 92 | 90 | 97.8 | 10000 | 10000 | 100 | |
| 4 | ሜይንስትሪሚንግ ስልጠና ማካሄድ | » | 1 | 1 | 100 | 5000 | 5000 | 100 | |
| 5 | የአቻ ለአቻ ስልጠና ማካሄድ | » | 121 | 121 | 100 | 6000 | 6000 | 100 | |
| 6 | በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ አውደ ጥናት | » | 3 | 3 | 100 | 10000 | 10000 | 100 | |
| 7 | የቤት ለቤት ተንከባካቢዎች ስልጠና .10 ቀበሌ ድፋፍ ሰጭ ኮሚተ ኮሚተ ስልጠና | » | 100<br>100 | 100<br>100 | 100<br>100 | 205500<br>30000 | 165755<br>30000 | 57<br>100 | |
| 8 | ስራ ማስኬጃ | ብር | - | - | | 16710.67 | 16709.6 | 100 | |
| 9 | ክትትልና ግምገማ | » | - | - | | 35500 | 22019.8 | 62.03 | |
| 10 | ደመወዝ | | | | | | | | |
| 10.1 | በክልል ጽ/ቤት | » | - | - | | 49500 | 49500 | 100 | |
| 10.2 | በወረዳ ጽ/ቤት | » | - | - | | 20700 | 20696.5 | 100 | |
| 10.3 | ለወረዳች የተለከ በጀት | | | | | 19820 | 17162 | 0 | |
| 11 | ገቢ ማስገኛ ስራ ድጋፍ | ቁጥር | 33 | 33 | 100 | 2000 | 2000 | 100 | |
| 12 | ኘሮጀክት ማስተዋወቂያ | አውደ ጥናት | 1 | 1 | 100 | 23100 | 16512.2 | 71.5 | |
| 13 | መኪና ጥገናና ሌሎች ወጪዎች | | | | 100 | 51160 | 34582 | 67.6 | |
| | ድምር | | 402 | 399 | 99.3 | 754991 | 677281.28 | 77.0 | |